# ቤተክርስቲያንን በኃይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት

# መምራት

## በፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት

Dynamic Churches
International

እግዚአብሔር እናንተን ማለትም የእርሱን ቤተክርስትያን እንድናገለግል አስደናቂ ዕድል ሰጥቶናል፡፡ ፍላጐታችን እናንተን የተሻለ ደቀመዝሙር ለማድረግ መርዳት ነው፡፡
ዳይናሚክ ቸርች ኢንተርናሽናል በትርፍ የማይሰራ ድርጅት ነው፡፡

*ተልዕኮአችን በቂ የተዘጋጁ ሰልጣኞችን በማፍራት እና መጋቢያንንና ክርስቲያን መሪዎችን በኃይል የሚንቀሳቀሱ ደቀመዝሙር አድራጊ አብያተክርስቲያናትን እንዲያኅለብቱ በመርዳት፣በየትኛውም የአለም ክፍል ባለ ሐገር ውሰጥ የሚገኘውን እያንዳንዱን ማህበረሰብ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መድረስ ነው፡፡*

እነዚህን የስልጠና ወርክሾፖች በመጠቀም ራዕይህን፣ግንዛቤህን፣ ብቃትህንና መተማመንህን በማሳደግ አለማቀፍ ደቀመዝሙር የማድረግ አገልግሎት ጀምረህ በአካባቢህ የሚገኙትን የብዙ ሰዎች ህይወት በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር እንድትለውጥ ፀሎቴ ነው፡፡ እግዚአብሔር በእንደዚህ አይነት አመቺ የታሪክ አጋጣሚ በአንድነት እንዳገናኘን በጣም እርግጠኛ ነኝ፡፡ እግዚአብሔር ለአለማችን ባለው ትልቅ አላማ ውስጥ፣እንደ ክርስቲያን ሁላችንም የየራሳችን ድርሻ አለን፡፡ ለደቀመዝሙርቱና ለእኛ የኢየሱስ የመጨረሻ ቃላትም ወደ ህዝቦች ሁሉ በመሄድ ደቀመዝሙር ማድረግ ነው፡፡ (ማቴ 28፡18-20) ይህንኑ ግልፅ የሆነ የመፅሀፍ ቅዱስ መመሪያ ብንከተል የታላቁ ተልዕኮን ተግባራዊ ልናደርግ እንችላለን፡፡

መሻታችን እግዚአብሔር ከፍ ብሎ እንዲከብር አንተን እንደ ግለሰብና እንደ ቤተክርስትያን ከእግዚአብሔር የተጠራህበትን ስራ እንድትፈጽመው መርዳት ነው፡፡

አል ሚድልተን

ስራ አስፈፃሚ

# በፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት አተገባበር።

1. የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን የሚያሳየውን ማሳያ ለመጋቢያን፣ ለቤተክርስትያን መሪዎች ወይም ፍቃደኛ ለሆነ ግለሰብ አካፍል /አሳይ/። (የ30 ደቂቃ ውይይት)
2. ለመቀጠል ፍቃደኛ ከሆኑ ለዳይናሚክ መሰረታዊ ወርክሾኘ - ክፍል አንድ ጊዜ ቀጠሮ መያዝ። (የ2 ሰዓት መርሃግብር)
3. ዳይናሚክ መሰረታዊ ወርክሾፕ - ትምህርት አንድ። ይህ ወርክሾፕ ከዚህ በፊት ለ30 ደቂቃ የተሰጠውን ማሳያ በመጨመር ለአንድ ሰዓት ተኩል የሚሆነውን የስልጠና ግዜ ያካትታል (በድምሩ 2 ሰዓት ኘሮግራም) በሚቀጥሉት ትምህርቶች ማለትም በትምህርት ሁለት፣ሦስትና አራት ሰልጣኞቹ እርስ በእርስ እንዲዛመዱ ማድረግ፤ ነገር ግን ስልጠናውን በሚወሰድበት ግዜ ግን እያንዳንዱ ሰልጣኝ የራሱን ደቀመዝሙር በመፈለግ ትምህርት አንድን ማስተማር መጀመር ይኖርበታል። ይህም የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ጅማሬ ይሆናል።
4. የዳይናሚክ መሰረታዊ ወርክሾኘ ከተሰጠ ከ 4-6 ሳምንት በኂላ ለዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ወርክሾፕ የሚደረግበት ቀን መወሰን።
5. ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ወርክሾፕን ማከናወን። (2 ሰዓት)
6. ልክ ለዳይናሚክ መሰረታዊ ወርክሾኘ እንዳደረግነው ተመሳሳይ የፈጣን ዕድገት መንገድ በመከተል ለዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ወርክሾፕን ማድረግ
7. በዚህ ግዜ ጉልህ የእንቅስቃሴ እድገት መታየት ይኖርበታል፤ ብዙዎች ሰዎችን በዳይናሚክ መሰረታዊ ትምህርት አንድ ወደ ክርስቶስ የሚመሩ ይሆናሉ፤ የደቀመዝሙርት ቁጥር ይጨምራል፤ ሁሉም ደቀመዝሙር - አድራጊ /የደቀመዝሙር መሪ/ ይሆናሉ (ደቀመዝሙር ከመሆን ባሻገር) እናም የትንንሽ ቡድን አስፈላጊነት ግንዛቤ ይፈጠራል አዳዲስ አማኞችና አዲስ ደቀመዝሙርትን ለመንከባከብ ይረዳ ዘንድ መሪዎችና ሌሎችም ቤተክርስትያን ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስትያን እንድትሆን የሚፈልጉበት ግዜ ይሆናል።
8. የህይወት ቡድን ወርክሾፕ የዳይናሚክ ማካፈል ወርክሾኘ እና ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ማስፋፊያ ወርክሾፕን ለማከናወን ቀን መወሰን። (ይህ በግምት የዳይናሚክ ደቀመዝሙር ወርክሾፕ ከተደረገ ከ 4 ሳምንት በኂላ) ( እያንዳንዱ ወርክሾኘ የ2 ሰዓት ሲወስድ፤ ሦስቱም ወርክሾኘ በአንድ ቀን ወይም በሦስት ተከታታይ ቀናት ሊሰጡ /ሊካሄዱ/ ይችላሉ።
9. ለመሪ ማኀልበት የታቀደ መርሃግብር ቀን መወሰን። የመሪነት ማሰልጠኛ መፅሀፍት፤ ተከታይ መሪዎችን ማሰልጠኛ፤ የህይወት ቡድን መሪ ማሰልጠኛና የመስካሪ ቡድን የአሰልጣኝ ማሰልጠኛና መፅሀፍቶቻቸው /ትምህርቶቻቸው/ መሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ ለማነፅ ይጠቀሙባቸዋል። ለበለጠ ግንዛቤ በእያንዳንዱ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኘውን መመሪያ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።
10. መጋቢያን ከሌሎች ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን ተግባራዊ ካደረጉ መጋቢያን ጋር በመገናኘት የመጋቢያን ህይወት ቡድን መመስረት ይኖርባቸዋል። ይህም እርስ በእርስ ለመመካከርና ለመበረታታት እንዲሁም በፈጣን ዕድገተ ደቀመዛሙርትን በአግባቡ ለማከናወን ይረዳቸዋል። ለዚህም አልፎ መድረስ - ቤተክርስትያን ለቤተክርስትያን መከታተያ የተሰገኘውን መፅሀፍ መጠቀም ይቻላል።

# የዚህ የስልጠና መፅሐፍ አጠቃቀም

ይህ የስልጠና መፅሐፍ ለማስተማር እንዲቻል ቀለል ያለ እና  በዚህ ስልጠና ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት የሰለጠኑት ሌሎችን ማሰልጠን እንዲችሉ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡

በተለያዩ በርካታ መንገዶች ይህንን መፅሀፍ መጠቀም ይቻላል፡፡ ከዚህ በሚከተሉት መንገድ መጠቀም ይቻላል፡፡

1. መፅሐፉን ለበለጠ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ደጋግሞ በማንበብ የራስህን የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር - የማድረግ ሂደትን በመጀመር፤ በዚህ መፅሀፍ ቅደም ተከተል ሌሎችን ደቀመዝሙር ማድረግ ትችላለህ/ሽ/፡፡
2. የአንድ ቤተክርስትያን መጋቢ ከሆንክ/ሽ/ ለሌሎች አብረውህ ለሚሰሩ መሪዎች ይህንን ራዕይ አካፍላቸው፡፡ ፍቃደኛ ከሆኑ ከእነርሱ ጀምሮ እነሱም አንዳቸው አንዳቸውን ደቀመዝሙር በማድረግ ይቀጥሉ፡፡ በዚህ መሰረት እራሳቸውን በብዙ ሰዎች እያበዙ ይሄዳሉ፡፡ ደቀመዝሙር የሚያደርጉ ሰዎች ሲበዙ ብቃት ያላቸው መሪዎች መታየት ይጀምራሉ፡፡ አንዳንዶቹም የራሳቸውን ህይወት ቡድን መስርተው ለመምራት ፍቃደኛ ይሆናሉ፡፡ የዚህን ግዜ በዚህ የስልጠና መፅሀፍ በቅደም ተከተል እንደተቀመጠው ወደ መሪነት ልታሳድጋቸውና የህይወት ቡድን በመመስረት ልታሰለጥናቸውና የሕይወት ቡድን በመመስረቱ ሂደት ልትመራቸው ትችላለህ፡፡ በተናጥልም ወይም በቡድን ስልጠናውን ልታደርግ ትችላለህ፡፡ ስለሆነም ቤተክርስቲያን እንዴት ደቀመዝሙር ማድረግ እንደምትችል ግንዛቤውም ልምዱም ያላቸው መሪዎች ይሆናሉ፡፡
3. ደቀመዝሙር በብዛት በማፍራት በርካታ ቡድኖች ሲመሰረቱና ውጤታማ ስትሆን ሌሎች መጋቢያን ተመሳሳይ ስራ ለመስራት እገዛ እንድታደርግላቸው መፈለግ ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት የሚያሳየውን ፓወርፖይንት ለማሳየት ጊዜ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ የተወሰኑ ያንተው ሰዎች የተወሰኑ የነርሱን ሰዎች ስልጠና ሊሰጧቸው ይችላሉ፡፡
4. ማህበረሰቡን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለመድረስ፣ በቂ መስካሪ ደቀመዛሙርት ያሏቸው በቂ ደቀመዝሙር አድራጊ አብያተክርስቲያናት እስከሚኖሩ ድረስ ይሄንን ራዕይ  ለሌሎች አብያተክርስቲያናት ማካፈል ተገቢ ይሆናል፡፡

### እንዴት ማስተማር ይቻላል፡፡

ስልጠናውን የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ፓወርፖይንት ራዕይ በማሳየት መጀመር፡፡ ዳይናሚክ መሰረታዊ፣ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ፣ የህይወት ቡድን እና ዳይናሚክ ማካፈል ወርክሾፕ መመሪያውን መከተል ይቻላል፡፡ ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን ለማስፋት በሚገልፀው ክፍል ስእላዊ መግለጫውን ልታብራራና ጥያቄዎችን ፅሑፉ በሚነበብበት ወቅት ግልፅ ለማድረግ ማብራራትና ዋና ነጥቦችን አፅንኦት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪ ብዙ ሃሳቦችን አለመጨመር ተገቢ ይሆናል፤ ምክንያቱም ውስብስብና ለግንዛቤ አስቸጋሪ ሊያደርገው ስለሚችል ነው፡፡ ለምታስተምረው ትምህርት የራስህን ስሜትና መገረም አካፍል፡፡ በመርህዎቹ ማዛመድ ሂደት ውስጥም እግዚአብሔር ህይወትን እንደሚቀይር የራስህን ምሳሌ ስለ መስጠትህ እርግጠኛ ሁን፡፡

### ወርክሾፑን እንዴት መጀመር እንደሚቻል

ወርክሾፑን እንዴት መጀመር እንደሚቻል የሚናገረው ክፍል ለአንተ የስልጠና መፅሀፉን ለሰልጣኞች ለማስተዋወቅና እንዴት አንድ ለአንድ ዳይናሚክ መሰረታዊ፣ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ፣ የህይወት ቡድን እና ዳይናሚክ ማካፈል ስልጠና ለመጀመር ልምድን ይሰጥሐል፡፡ እያንዳንዱ ወርክሾፕ 2 ሰዓት ሊወስድ ይገባል፡፡

የደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትህን የማስፋት ወርክሾፕ ዳይናሚክ መሰረታዊ፣ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግና እና ዳይናሚክ ማካፈልን በትንንሽ ቡድኖች የህይወት ቡድን ይፈጥሩ ዘንድ በማጣመር ቤተክርስቲያን ውጤታማ ደቀመዝሙር አድራጊ እንድትሆን ፅንሰ ሃሳቡንና ስልቱን ያጎለብታል፡፡ እያንዳንዱን ቡድን ወደ ብዙ ቡድኖች ለማጅ መሪዎችን ለማጎልበት የተያዘውን ስልት በቅደም ተከተል በመከተል ማፍራት ይቻላል፡፡ ይህ ወርክሾፕ 2ሰዓት ይወስዳል፡፡

# ቤተክርስትያንን በኃይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት መምራት

ይህ መጽሐፍ ***ቤተክርስትያንን በኃይል ወደ ተሞላ ሕይወት መምራት*** በተሰኝ ርዕስ ከሚሰጡ በርካታ ትምህርቶች አንዱ ነው። እያንዳንዱ የፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወርክሾፕ እንዴት ከጠቅላላው ሰዎችን ለሚፈለገው አላማ ለማጎልበት ከተያዘው ስልት ጋር እንደሚዛመድ የሚከተለው ነጥብ ያሳያል።

| **የስልጠና መፅሀፍ** | **ስልጠናው የሚሰጠው ሰው** |
|---|---|
| 1. የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ስልጠናና ወርክሾኘ | - ለመጋቢያንና ለመሪዎች አንድ ለአንድ ደቀመዝሙር የማፍራት እና ትንንሽ ቡድኖችን ለማብዛት<br>- ከላይ የተጠቀሱትን ወደ ህይወት ቡድንነት ለማቀናጀት<br>- አገልጋዮችን ለማሳደግና የህይወት ቡድኑን በማስፋፋት ቤተክርስትያንን ደቀመዝሙር የምታፈራ ለማድረግ |
| 2. መምራትን መማር<br>- የተተኪ መሪ ስልጠና | - የህይወት ቡድን መሪዎች ተተኪዎቻቸውን ሲያሰለጥኑ የሚጠቀሙበት |
| 3. የሚመሩ መሪዎች<br>- የህይወት ቡድን መሪ ማሰልጠኛ | - አሰልጣኞች የህይወት ቡድን መሪዎቻቸውን ሲያሰለጥኑ የሚጠቀሙበት |
| 4. የአሸናፊዎች ቡድን<br>- የአሰልጣኞች ማሳደጊያና ማስተማሪያ | - መጋቢያን አሰልጣኞቻቸውን ለማሳደግ የሚጠቀሙበት |
| 5. አልፎ መድረስ<br>- ቤተክርስትያን ለቤትክርስትያን መከታተል | - በክልል ወይም በአለምአቀፍ ደረጃ መጋቢያንና መሪዎች ሌሎች ቤተክርስትያናትን ለማገዝ የሚጠቀሙበት |

**እነዚህ ሁሉ መጽሐፍት በቢሮአችን ወይም ከታች በተቀመጠው መረጃ መረባችን በኩል ይገኛሉ።**


*Dynamic Churches International*
**International/Canadian Address:**
164 Stonegate Close,
Airdrie, Alberta, Canada, T4B 2V2
(403) 912-4438
dcimiddleton@shaw.ca
www.dynamicchurches.org


እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።


Copyright © 2009 Dynamic Churches International.
All rights reserved including translation.
ከዚህ መጽሐፍ ማንኛውንም ክፍል መግለበጥም ሆነ ማባዛት ያለ ጽሑፍ ፍቃድ የተከለከለ ነው። ይሁንና ከዚህ መጽሐፍ በግል ለመጠቀም ቅያችን መገልበጥ ይቻላል።

# በፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት

## ማውጫ

## ወርክሾፖችን የመጀመሪያ መንገድ

*ርዕስ* *ገፅ*


| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| በፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሒደት | 7 |
| የዳይናሚክ መሰረታዊ ወርክሾፕ መመሪያዎች | 16 |
| የዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግ ወርክሾፕ መመሪያዎች | 17 |
| የጀማሪ ህይወት ቡድን ወርክሾፕ መመሪያዎች | 18 |
| የዳይናሚክ ማካፈል ወርክሾፕመመሪያዎች | 28 |
| የደቀመዝሙር የማፍራት ሂደትህን የማስፋፋት ወርክሾፕ | 37 |
| የህይወት ቡድን መሪዎች ኃላፊነት | 43 |
| የምስክር ወረቀት | 43 |


*«ቤተክርስትያንን በኃይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት መምራት»*

# በፈጣን ዕድገት

# ደቀመዝሙር የማድረግ

# ሒደትን ለማጎልበት

## ወርክሾፖችን የመጀመሪያ መንገድ

*«ቤተክርስትያንን በኃይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት መምራት»*

# በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሒደት

***መግቢያ፡-***

እንደ ደቀመዝሙር እና እንደ ደቀመዝሙር አድራጊ የሚከተሉትን ነጥቦች እንዴት በጣም የተሳካ አገልግሎትና ህይወት መምራት እንደምትችል ግንዛቤ ይሰጡሃል፡፡ በተጨማሪም ቤተክርስትያንህን የዲ.ሲ.አይን በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን በመጠቀም ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስትያን መሆን እንደምትችል ለማገዝ ይረዱሃል፡፡

## እስቲ ይህን አስብ

- ለመጀመሪያ ግዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ስትቀበል ከአጠገብህ ሆኖ እንዴት በአገኘኸው አዲስ ህይወት መኖር እንዳለብህ ግንዛቤ የሰጠኽ ሰው ማን ነበር? ይህንን ግለሰብ ታውቀዋልህ?
- በህይወትህ ምን አይነት ጉልህ አስተዋፅዎ አድርጐ ነበር?
- ምንም አይነት ሰው ካልነበረህ ክርስትና ህይወትህ እንዴት ነበር የተስተጓገለው?
- ሌሎች ግለሰቦችን በክርስትና ህይወታቸው ጉዞ  አግዘህ ታውቃለህ?

## ትልቁን ስዕል መመልከት

### የእግዚያብሔር ዘላለማዊ ሐሳብ /እቅድ/ የጠፋውን አለም ለማዳን ነው፡፡

*«የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው፡፡»* ሉቃ 19÷10

ኢየሱስ እንዲህ አለ፡-

*«አባት ሆይ የሰጠኸኝን ስራ በመፈጸም በምድር አከበረሁህ»* ዮሐ 17÷4

**አስብ፡-**

እግዚያብሔር በዚህ ባለህበት ስፍራ ውስጥ ተገኝቶ ***«እንደ ግለሰብ ወይም እንደ ቤተክርስትያን የሰጠሁህን ስራ ፈፅመሃል?»*** ብሎ ቢጠይቅህ መልስህ ምን ይሆን?

**እግዚያብሔር ለህይወትህ ወይም ለቤተክርስትያንክ ያለውን ዓላማ ተረድተሃል?**

## የእግዚያብሔር ዓላማ ለቤተክርስትያን

ኢየሱስም እንዲህ አለ፡-

***«...አብ እኔን እንደ ላከኝ እኔም እናንተን እልካተኋለሁ»*** ዮሐ 20÷21

- የእግዚያብሔር ኃይል፡- ወንጌል - ሮሜ 1÷16
- የእግዚያብሔር ዓላማ ለቤተክርስትያን፡- ወንጌሉን ማዳረስ - ሉቃ 19÷10
- የእግዚያብሔር ስልት፡- ህዝቦችን ሁሉ ደቀመዝሙር ማድረግ - ማቴ 28-10÷20

## የእግዚያብሔር ትዕዛዝ

***«ጌታ አምላክህን በፍጽም ልብህ ፣ በፍጽም ነፍስህ፣በፍጽም ሐሳብህ ውደድ…ጐረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ»*** ማቴ 22÷18-20

### የእግዚያብሔር ታላቁ ተልዕኮ

***«ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅድስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዝሙር አድርጓቸው፤ ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፡፡»***

ማቴ 28÷18-20

**ደቀመዝሙር ማን ነው?**

- ጌታን እንደ ግል አዳኙ የተቀበለ ሁሉ ደቀመዝሙር ነው?

**ደቀመዝሙር፡-**

- ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ ተቀብሎ በእርሱ ትምህርት የሚኖር ነው።
- ደቀ መዝሙር ክርስቶስ እንደኖረው የሚኖር ነው እንጂ ስለክርስቶስ ብቻ የተማረ አይደለም።

## የእድገት መርህ

ጤናማ ህይወት ያላቸው ፍጡራን ሁሉ ያድጋሉ።
እግዚአብሔር ፍጥረቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለመተላለፍ ብቃት ባላቸው ህያው አካላት እንዲያድጉና እንዲራቡ አድረጎ ፈጥሯቸዋል። **ቤተክርስቲያን ህይወት ያላት አካል ነች**

## ስጋዊ ቤተሰብ

አስቲ እንዴት በስጋ እንደምናድግ እንመልከት

ህፃን ⇒ ልጅ ⇒ ወጣት ⇒ ያላገባ ጉልማሳ ⇒ ያገባ ⇒ ህፃን ⇒ ልጅ ⇒ ወጣት

እድገት ጥሩ የሚሆነው በቤተሰብ ውስጥ ነው። ነገር ግን በተጨማሪም የአንድ ለአንድ ክትትልና እንክብካቤ ይጠይቃል።

---

## መንፈሳዊ ቤተሰብ

መንፈሳዊ እድገት በተሻለ ሁኔታ እንዲመጣ ከተፈለገ መንፈሳዊ የቤተሰብ አውድ ወሳኝ ይሆናል። ነገር ግን ይህም የአንድ ለአንድ ክትትልና እንክብካቤ ማድረግን ይጠይቃል።

አዲስ ክርስቲያን ⇒ ደቀመዝሙር ⇒ ደቀመዝሙር አድራጊ ⇒ መሪ ⇒ አዲስ ክርስቲያን ⇒ ደቀመዝሙር ⇒ ደቀመዝሙር አድራጊ

ሰዎች ትኩረታቸውን የራሳቸውን ፍላጐት ከሟሟላት ላይ አንስተው የሌሎችን ፍላጐት ለሟሟላት ትኩረታቸው ሲያደርጉ የዚያን ግዜ የእድገት ምልክትን አሳይተዋል ሊባል ይቻላል።

# ቤተ-ክርስቲያን የተያያዘ መንፈሳዊ ቤተሰብ መሆን ይገባታል!

*ብዙ አብያተክርስቲያናት መንፈሳዊ ቤተሰብ ከመምሰል ይልቅ መንፈሳዊ እንስማውታ መስለዋል፡*

### መንፈሳዊ ልጆች


መንፈሳዊ ልጆች የሚያመለክተው በደቀመዝሙሩና በደቀመዝሙር አድራጊው የሚደረገውን አረባብ ማለታችን ነው።

- በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ያሉ አማኞች ወደ ሙሉ የተሰጡ የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ደቀመዝሙርነት ተለውጠዋል?
- ወንጌልን ይሰብካሉ?
- ሌሎች መንፈሳዊ ልጆችን በማስታጠቅ እራሳቸውን የሚያራቡ ናቸው?

እንደዚህ አይነት ቤተክርስትያን እንዴት ሊከሰት ይችላል?

# ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት

በመንፈሳዊ ቤተሰብ ውስጥ ማደግ ከተፈለገ ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን ማጉልበት ወሳኝ ነው።




ስዕላዊ መግለጫውን በምታጠኑበት ግዜ የቀስቶቹን አቅጣጫ ልብ ብለህ ተመልከት

**የኢየሱስ ክርቶስን ወንጌል ለሌሎች በምናካፍልበት ጊዜ**

***ሂደቱ በእግዚአብሔር ዓላማ ይጀመራል።***

1. በወንጌል ከተደረሰ በኂላ፣ **አዲሱ ክርስቲያን መመገብ ያስፈልገዋል**
   *በመሰረታዊ የክርስትና ትምህርትም ስናሰለጥነው ሂደቱ ይቀጥላል።*

## 2. የሰለጠኑ ደቀመዛሙርት

*እራሳቸውን እንዲያባዙ ሆነው ስለሰለጠኑ፣*

***ለማፍራት የታጠቁ ናቸው።***

## 3. ሌሎችን የሚያሰለጥኑ ደቀመዝሙር አድራጊዎች

***የመሪ መጎልበትና መተካት***

ራሳቸውን እንደ *«ታማኝና ለማስተማር እንደሚችል»* (2 ጢሞቲዎስ2÷2) ካሳዩ በኋላ በተለየ አገልግሎት ማገልገል ይችሉ ዘንድ ለበለጠ <u>መታጠቅ</u> <u>የተዘጋጁ</u> ይሆናሉ።

*አሁን እነዚህ የሚራቡ ደቀመዝሙር አድራጊዎች*

## 4. *አገልግሎቱን የሚያስፋፉ መሪዎች*

*ሲሆኑ፣ ሂደቱ እየተስፋፋ ይሄዳል።*

*ማስታወሻ፦ በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለሌሎች ማካፈል ዋና ትኩረት ነው!*

በአንድ እጅህ ስዕሉን በተራቁጥር 1 እና 4 ያሉትን ክቦች በመተው ሸፍን። ብዙ አብያተክርስቲያናት እየሰሩ ያሉት በ1 እና በ4 ውስጥ ያሉትን ብቻ ነው።

- አዳዲስ ሰዎችን በወንጌል እንደደረሱ ወዲያው ወደ አገልግሎት ያስገቧቸዋል
- በ 2ኛውና 3ኛው ሂደት ውስጥ ሳያልፉ፣ ሰዎች በፍፁም ወደ መሪነት ሊሸጋገሩ አይችሉም።
- የአገልግሎት ክፍሎች ለደህንነታቸው እንኳን እርግጠኛ ባልሆኑ ሰዎች ይሞላሉ።
- ምናልባትም እንዴት በፀሎት ከጌታ ጋር መገናኘት እንደሚችሉ እንኳ ላያውቁ ይችላሉ።
- ምናልባትም በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላት ላያውቁ ይችላሉ።
- ለሌሎች ወንጌሉን የማካፈሉም ነገር አጠራጣሪ ነው የሚሆነው

*አገልግሎታቸው ምን ያህል ውጤታማ ይሆናል ብለህ ታስባለህ?* ____________________

*ይህ የአንተን የቤተክርስቲያን ገፅታ ያሳያል?* ________________________________

## ለታላቁ ተልዕኮ ዕውን መሆን ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወሳኝ ነው

**ቅዱሳንን ማዘጋጀት**

***«አንዳንዶቹን ኃዋሪያት ሌሎቹን ነቢያት፣ አንዳንዶቹን ወንጌል ሰባኪያን፣ ሌሎቹን ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤ ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፤ቅዱሳንን ለአገልግሎት ስራ ለማዘጋጀት ሲሆን ----»*** (ኤፌ4-11-12)

ቤተክርስትያን ሰዎችን ለእድገት እንደምታሰማራ ሆና መዋቀር አለባት!

## ቅዱሳንን ማሰማራት

ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን በቂ የሆኑ መስካሪ ደቀመዛሙርትን በማፍራት ለእያንዳንዱ ማህበረሰብ እና ለአለም የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በማድረስ የታላቁ ተልዕኮን ግብ ዕውን ለማድረግ የምትተጋ ነች!

## ምን ያህል ደቀመዝሙርና ደቀመዝሙር አድራጊዎች ያስፈልጉሃል?

- የከተማህ ወይም ያለህበት ህብረተሰብ የህዝብ ብዛት ምን ያህል ነው? ______________
- እያንዳንዱ መስካሪ ደቀመዝሙር ለ9 ሰዎች ወንጌሉን ቢያካፍል (ወይም አንዱ ለ 10) ____________________የሚያህሉ መስካሪ ደቀመዝሙር ያስፈልጉሃል።
- ጠቅላላ ከተማህን ወይም አካባቢህን ለመድረስ ምን ያህል ደቀመዝሙር አድራጊ አብያተክርስትያን ያስፈልጉሃል? _______________________

## እንዴት አድርገን እንደዚህ ያለ የደቀመዝሙር ሰራዊት ማስነሳት እንችላለን?

## በሚከተለው መልኩ መጀመር ትችላለህ

በእያንዳንዱ መፅሀፍ ጀርባ የሚገኘውን የመሪ መመሪያ በማንበብ በራስህ ልትጀምር ትችላለህ ደግሞም በቤተክረስቲያንህ ወይም በአካባቢህ ካሉ ሌሎች ሰዎች ጋር ከዚህ በታች ያሉትን ወርክሾፖች ለመካፈል መዘጋጀት ትችላለህ።

- የ2ሰዓት  የዳይናሚክ መሰረታዊ ትምህርት ወርክሾፕ መካፈል፤በመቀጠልም ከ 4-6 ሳምንት በኃለ
- የ2ሰዓት ዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግ  ወርክሾፕ  በመካፈል መቀጠል ትችላለህ።

ማስታወሻ፡-ለበለጠ መረጃ በመረጃ መረባችን ላይ www.dynamicchurches.org ያሉተን ኮርሶች ልታገኝ ትችላለህ።

በራስህም ወይም የዳይናሚክ መሰረታዊ ትምህርት  ወርክሾፕን በመውሰድ  የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደቱን መጀመር።

## የፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን አካሄድ

አንተ ወይም ከናንተ አንዱ በዳይናሚክ መሰረታዊ አንድን ሰው ያሰለጥናል። ያ ሰው እንደገና አንድ ሰው በመፈለግ ሌላ ሰው በዳይናሚክ መሰረታዊ ትምህርት አንድ ያሰለጥናል። በመቀጠል ሁለተኛውን ክፍል በመቀጠልና አራቱንም ክፍለ ጊዜዎች በማስተማር ደቀመዝሙርህን ታሰለጥናለህ። እያንዳንዱ ሰልጣኝ ሌላውን በሚያሰለጥንበት ጊዜ በየጊዜው አዲስ ደቀመዝሙርና ደቀመዝሙር አድራጊ እየተጨመሩ ይሄዳሉ! ለዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግም በተመሳሳይ መልኩ ታደርጋለህ።

## በዚህ መልኩ ስትሰራ ያለውን አቅም ተመልከት

- በዳይናሚክ መሰረታዊ (አራት ትምህርቶች) እና በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ (9 ትምህርቶች) በጠቅላላው 13 ትምህርቶች አንድን ሰው ታሰለጥናለህ (አንተ የምታሰለጥነው የመጀመሪያውን ሰው ብቻ ይሆናል እያንዳንዱ ሰው በአንድ ግዜ አንድ ሰው ብቻ ያሰለጥናል) እንበል።
- በዚህ መንገድ በዚህ አንድ አመት ውስጥ ሦስት ተጨማሪ ሰዎችን ማሰልጠን ትችላለህ። እያንዳንዳቸው በአማካይ በየሳምንቱ አንድ ሰው ለማሰልጠን ቢጀምሩ በሚቀጥለው አመት መጀመሪያ ላይ 52 አዳዲስ ደቀመዛሙርት ማሰልጠን ይቻላል።
- የሚጀምሩበት ግዜ በአማካኝ ከሁለት ሳምንት በኋላ ከሆነ በዓመት 26 አዳዲስ ደቀመዝሙር ማፍራት ይቻላል።
- የሚጀምሩበት ግዜ በአማካኝ ከ 4 ሳምንት በኋላ ከሆነ በዓመት 13 አዳዲስ ደቀመዝሙር ማግኘት ይቻላል።
- ይህንን ውጤት ሰዎችን ደቀመዝሙር እንዲያደርጉ በምታበረታታቸው ሰዎች አባዛው። በጠቅላላው _____________

### እነዚህን አዳዲስ ደቀመዝሙር እንዴት ልትንከባከብ ትችላለህ?

አንድን ሰው ካሰለጠንክ በኋላ ለመመገብና ለመከታተል የሚረዳ ህይወት ሰጪ አካባቢን ከ13 ደቀመዝሙር ውስጥ ፍቃደኛ የሆኑትን እነዚያን ከ8-10 የሚደርሱ ሰዎችን በመያዝ የህይወት ቡድን መመስረት ትችላለህ። አንተ ወይም ሌላ ሰው ይህንን ቡድን ሊመራ ይችላል።


### ውጤታማ ደቀመዝሙር አድራጊ የህይወት ቡድን

የህይወት ቡድን የፍቅርና እንክብካቤ ቦታ በመሆን እያንዳንዱ ሰው ጤናማ ዕድገት እንዲያመጣ ሆኖ የተዘጋጀ ነው። ለአዳዲስ ሰዎች አመቺና ተስማሚ የሆነ ነው። ለእያንዳንዱ የቡድን አባላት ቀላልና ተወዳጅ ስፍራ የሆነና ጓደኞቻቸውን ወደ ቡድን ለመጋበዝ በሚያመች መልኩ የተዘጋጀ ነው።

## የህይወት ቡድን የሚያጠቃልላቸው

1. መሪ
2. እንግዳተቀባይ
3. አዲስ ክርስቲያን
4. ቤተክርስቲያን ጉቡኚዎች
5. ተተኪ መሪ
6. ከየትኛው የዕድገት ደረጃ ያሉ ፈቃደኛ የሆኑ ክርስቲያኖች
7. ተጋባዥ ወይም ከላይ የተቀመጡት ሰዎች ጓደኞች
8. ባዶ ወንበር አዲስ ለሚመጣ ሰው

የህይወት ቡድኑ በተራ ቁጥር 1-2-5 ና 6 ባሉት አራት ሰዎች ሊጀመር ይችላል።




በርካታ ሰዎች በዳይናሚክ መሰረታዊና በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ከሰለጠኑ በኋላ የመጀመሪያው የህይወት ቡድን ሊሆኑ ይችላሉ።

በፊተኛው ገፅ ላይ በስዕሉ እንደሚታየው መሪው ተተኪውን በዳይናሚክ ማካፈል ያሰለጥነዋል፡፡ይህ የሚሆነው አንድ ለአንድና ከቡድኑ መሰብሰቢያ ጊዜ ውጪ ይሆናል፡፡ ቤተክርስቲያን ተመላላሽ ሆነው ድነት ያላገኙ ሰዎች ሲጉበኙ ወንጌሉን የመካፈል ዕድል ያገኛሉ፡፡ እያንዳዱም ሰው ወደ ትንሹ ቡድን እንዲመጣ መጋበዝ ይኖርበታል፡፡ ከተጉብኚዎቹ አንዱ ደህንነት ካገኘ ወይም ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ከተቀበለ እንደ አዲስ ክርስቲያን በዳይናሚክ መሰረታዊ እንዲሰለጥን ይበረታታል፡፡ ይህንን ኃላፊነት በተራ ቁጥር 6 የተቀመጡት ክርስቲያኖች ይወስዳሉ፡፡ ልክ የዳይናሚክ መሰረታዊ ትምህርት እንዳበቃ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ በአስተናጋጁ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ከመሪ የመሪነት ስልጠና ያጠናቀቀው ተተኪ መሪውም የዳይናሚክ ማካፈልን ስልጠናን በመሰጠት ይቀጥላል፡፡

## የህይወት ቡድን ለእያንዳንዱ የቡድኑ አባል አገልግሎትን እንዲለማመድ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡

# አንድ ለአንድ + ትንሹ ቡድን = የህይወት ቡድን፡፡

## የመጨረሻው ውጤት

እያንዳንዱ የህይወት ቡድን አባል ለአዳዲስ ሰዎች ክርስቶስን ሲያካፍል፣ ክርስቶስን የተቀበሉት ደቀመዝሙር ሲሆኑ፤ መሪዎች እያደጉ ይመጣሉ፤ እግዚአብሔርም ቤተክርስቲያን እንድታድግ ያደርጋታል፡፡

***«እኔ ተክልሁ፥ አጵሎስ ውሃ አጠጣ ያሳደገው ግን እግዚአብሄር ነው»*** 1ቆሮ 3÷6

የህይወት ቡድኖች መራባት በርካታ ጥራት ያላቸው ደቀመዛሙርት ሊያስገኝና ብዙ ሰዎችም ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ያስችላል፡፡

እግዚአብሔር በቤተክርስቲናችሁ ውስጥ ምን ሊያደርግ ይሆን!

እርዳታ ካስፈለጋችሁ እባካችሁ አግኙን፡፡

# በፈጣን ዕድገት

# ደቀመዝሙር የማድረግ

# ሒደት ወርክሾፖች

*«ቤተክርስትያንን በሐይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት መምራት»*

# የወርክሾፕ አሰልጣኞች መመሪያ

*ማሳሰቢያ፡- መጋቢው ወይም መሪው ዳይናሚክ መሰረታዊ ወይም ዳይናሚክ ደቀመዘሙር ማድረጊያውን በመጠቀም ሰዎችን ለማሰልጠን መጀመር ይችላል። እያንዳንዱ የሰለጠነ ግለሰብ ደግሞ ሌሎችን በማሰልጠን ይቀጥላል። በተጨማሪም ይህንን የወርክሾፕ ፎርም በመጠቀም ጥንድ ጥንድ ሆነው የተቀረውን ትምህርት ከወርክሾፑ በኋላ ሊጨርሱ ለተዘጋጁ በርካታ ሰዎች ወርክሾፕ በማድረግ የፈጣን ዕድገት ሂደቱን ሊጀምር ይችላል።*

# ዳይናሚክ መሰረታዊ ወርክሾፕ (2 ሰዓት)

- **በፀሎት ጀምር**
- ***እያንዳንዱ ሰው መሪውን ጨምሮ የዳይናሚክ መሰረታዊ መፅሀፍ መያዛቸውን አረጋግጥ***
- ***የመሪዎች መምሪያ የት ቦታ እንደሚገኝ አሳያቸው***
- *የመሪዎች መምሪያ የተሰኘውን ክፍል በሙሉ አንብብላቸው።* ***ዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግ ዕድልና የምስክር ወረቀት*** ከአራቱ ትምህርቶች መጨረሻ እንደሚገኝ ጠቁማቸው።
- አንድ ተሳታፊ በመምረጥ ***የዳይናሚክ መሰረታዊ*** ትምህርት አንድን በመምረጥ **አሳያቸው**
  - እራስህን አስተዋውቅ
  - ወደ ትምህርት አንድ ምራቸው
  - ነጥብ 1 እና 2ን ሸፍን (ሌሎች ሰልጣኞችም አብረውህ ነጥብ አንድና 2 ያጠናቅቁ)
  - ሰልጣኞች ጥንድ እንዲሆኑ እርዳቸው (ሴት ከሴት ወንድ ከወንድ ጋር)

***ማሳሰቢያ፡-አሰልጣኞች ከአንድ ተሳታፊ ጋር በጥንድ ለመሆን ወይም ከአንድ ጥንድ ጋር ሦስተኛ ሆኖው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።***

- **ጥንዶች ማን እንደ አዲስ ክርስቲያን ማን ደግሞ እንደ ደቀመዝሙር አድራጊ እራሳቸው እንዲሆኑ ከወሰኑ በኋላ፣**
- የትምህርት አንድን ከአቆሙበት በመቀጠል እንዲጨርሱ አድርግ።
- የትምህርት አንድን ጥያቄዎች በሚሰሩበት ግዜ **በአጠገባቸው በመሆን እርዳቸው።**
- ጥያቄዎቹን እንደጨርሱ ወደ ትምህርት አንድ **የጥያቄ መልስ በመሄድ** ጥያቄዎቹን በትክክል መመለሳቸውን ያረጋግጡ።
- **በዚህ ጊዜ ጥያቄ እንዲጠይቁ እድል ስጣቸው።**
- **እንደገና ቡድኑን በመሰብሰብ ማን ደቀመዝሙር ማድረግ እንዳለበት ወስን**
  ከወርክሾፑ በኋላ ______________________ __________________ ን ያሰለጥናል
  ከወርክሾፑ በኋላ ______________________ __________________ ን ያሰለጥናል
  ከወርክሾፑ በኋላ ______________________ __________________ ን ያሰለጥናል
- ***ሌላ የዳይናሚክ መሰረታዊ ወርክሾፕ ለማድረግ ዕቅድ ካለህ***
  *ቀን* __________________*ሰአት*___________________ *ቦታ* __________________
- ***ከስልጠናው ሳምንታት በኋላ የአራቱንም ትምህርቶች ይጨርሱ ዘንድ እያንዳንዱ ተጓዳኝ ለመገናኘት ቀንና ጊዜን ለመመደብ እንዲችል ዕድል ስጣቸው። እርስ በርሳቸው ይህንን እየሰሩ እያንዳንዱ ተጓዳኝ የራሱን ደቀመዝሙር መምረጥ ይኖርበታል። ደቀመዝሙር የሚሆን ሰው አዲስ ክርስቲያን፣ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው፣ ወይም ደግሞ የበረታ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል፤ ከትምህርት አንድም ይጀምሩ።***
- ***እርስ በእርሳቸው ከፀለዩ በኋላ መርሃግብሩን በፀሎት ዝጋው።***

# የዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ወርክሾፕ (2ሰዓት)

- በፀሎት ጀምር
- በርከት ያሉ ሰዎችን ይዘህ ከዳይናሚክ መሰረታዊ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ አድርግ
- እያንዳዱ ሰው የዳይናሚክ ማሰልጠኛ ከጠቅላላ መምሪያው ጋር መያዙን አረጋግጥ ይህም ከዳይናሚክ መሰረታዊ መጨረሻ ላይ እንደሚገኝ አሳያቸው
- ያለምንም ገለፃ ጠቅላላ መምሪያውን አንብብ
- በጥንድ እንዲቀመጡ አድርግ (ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት)
- ማን ደቀመዝሙር ማን ደግሞ ደቀመዝሙር አድራጊ መሆን እንዳለባቸው እንዲወስኑ አድርጋቸው።

***ማስታወሻ፦ በትክክለኛ የደቀመዝሙር አደራረግ ልምምድ አንድ ትምህርት አንድን የተካፈለ ደቀመዝሙር አድራጊ እና ይህንን ትምህርት ለመጀመሪያ ግዜ የሚወስድ አንድ ደቀመዝሙር መኖር እንዳለበት ግለጽላቸው፤ ሆኖም በዛሬው ወርክሾፕ ደቀመዝሙር አድራጊዎቹ ትምህርቱን በራሳቸው ባለማጠናቀቃቸው፣ ሁለቱም አብረው እንደሚማማሩ ግለፅላቸው።***

- ገፅ 1ን እንዲገልፁ ካደረግሃቸው በኋላ ትምህርት አንድን አውጥተው የሚከተለውን አጀንዳ እንዲከተሉ አድርግ፤ እያንዳንዱን ትዕዛዝ (ስራ) ከፈፀምክ በኋላ ለማረጋገጥ ይህንን ምልክት (✓) ምልክት አድርግ። በዚህ ጊዜ የምትችለውን ያህል ድረስ ሂድ።
- ***እየሱስን እንደ ግል አዳኜ ማወቅ*** የሚለውን በሦስተኛው ገፅ ላይ የሚገኘውን ትምህርት አንድ እንዲሰሩ አድርጋቸው።
- የወርክሾፕ አሰልጣኙ ማንኛውም የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስና የሚሰሩትን ለመመልከት በአጠገባቸው በመመላለስና በመገኘት እርዳቸው፤ እያንዳንዱም ሰው ጥንድ ሆኖ እንደተቀመጠና ትምህርት አንድን እያጠና እንዳለ አረጋግጥ።
- የስልጠናው ጊዜ እንዳለቀ እንደገና ሰብስባቸው፤ በአንዳንድ መልሶቻቸው ላይም በመወያየት ሌሎችን ደቀመዝሙር ማድረግ መቻላቸውን መተማመን እንዲሰማቸው ያደረጋቸዋል።
- በዚህ ጊዜ ጥያቄ እንዲጠይቁ እድሉን ስጣቸው።
- ቡድኑን ወደ ነበረበት እንዲመለስ በማድረግ ማን ደቀመዝሙር እንደሚያደርግ ወስን።
  ከወርክሾፕ በኋላ ________________ ___________________ን ደቀመዝሙር ያደርጋል
  ከወርክሾፕ በኋላ ________________ ___________________ን ደቀመዝሙር ያደርጋል
  ከወርክሾፕ በኋላ ________________ ___________________ን ደቀመዝሙር ያደርጋል
- የትምህርት ሁለት የመዘጋጃ ስራ አውጥተህ ተመልከት፤ ትምህርት ሁለት ከአጋራቸው ጋር በሚቀጥለው ጊዜ ከመገናኘታቸው በፊት መጠናቀቅ ይኖርበታል። (ምናልባት ትምህርት አንድን በመጀመሪያ ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል)።
- ከወርክሾፕ ስልጠና በኋላ የተቀሩትን ትምህርቶች ይጨርሱ ዘንድና የሚገናኙበትን ቀኑንና ጊዜውን እንዲያመቻቹ እድሉን ስጣቸው። ልክ እንደ ዳይናሚክ መሰረታዊ እያንዳንዱ ሰው አንድ ሰው በመፈለግ ከዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ትምህርት አንድ በመጀመር ማሰልጠን ይኖርበታል። የተቀሩትን ትምህርቶች ለማጠናቀቅ ከተጓዳኞቻቸው ጋር ይስሩ።
- ምናልባት ሌላ የዳይናሚክ ማሰልጠኛ ወርክሾፕ ለማድረግ እቅድ ካለህ
  ቀን _______ሰዓት ____________________ ቦታ _________________________
- ከተጓዳኞቻቸው ጋር በፀሎት እንዲሆኑ ካደረግህ በኋላ በፀሎት ኘሮግራሙን ዝጋው።


# ለጀማሪ ህይወት ቡድንህ መጀመሪያ የሚሆን ተግባራዊ ወርክሾኘ (2 ሰዓት)

***የዳይናሚክ መሰረታዊና የዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግን*** ካጠናቀቅህ በኋላና ***የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር ማድረግን*** አስደናቂነት ከተለማመድህ በኋላ፣ እነዚህ እያደጉ የሚመጡትን ደቀመዝሙር ለመንከባከብ ይረዳ ዘንድ የቡድን መመስረቱ አስፈላጊነት አሁን መገንዘብ ትጀምራለህ። በተጨማሪም **ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን** የመሆን አቅም እንዳለ ታያለህ። በደህና መጀመርህ ደግሞ ወሳኝ ነው። **ጀማሪ ቡድኖችን** ለመጀመር ስትነሳ ይህ ወርክሾኘ ልምድንና መተማመንን ይሰጥሃል።

## ስም ምንድን ነው?

ምናልባት ትንንሽ ቡድን ወይም የቤት ለቤት አገልግሎት አስቀድሞ ሊኖርህ ይችላል። በጣም ወሳኝ የሆኑትን ግብአቶች የአንድ ለአንድ ማሰልጠኛና የመሪ ማሳደጊያ ከሌሉህና እነዚህን ቁምነገሮችን ለመጨመር ከፈለግህ ለአዲሱ ቡድን ለየት ያለ ስም መምረጥ ይኖርብሃል። **ስሙ ተመሳሳይ እስከሆን ድረስ የሰዎችን አስተሳሰብ ለመቀየር አስቸጋሪ ይሆናል።** የምትፈልገውን አይነት ማንኛውንም ስም ልትጠቀም ትችላለህ ነገር ግን የሚከተሉት አስተያየቶች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብሃል።

***የህይወት ቡድን*** የሚባለው አሰያየም ዋና ***የደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን*** አካላትን ይወክላል። ለምሳሌ




## አንድ ለአንድ ስልጠና + ትንሹ ቡድን = *የህይወት ቡድን*

በዚህ ወርክሾኘ **የህይወት ቡድን ትንሽ ቡድን** ክፍለግዜን እንለማመዳለን

## ትንንሽ ቡድኖችን ለመጀመር

*የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን የተለማመዱ ሰዎችን በመምረጥ በጀማሪ ቡድን ውስጥ እንዲሳተፉ አዘጋጃቸው፡፡ (በቂ የተሰጡ መሪዎች ካሉህ ከአንድ በላይ በሆነ ቡድን ልትጀምር ትችላለህ)*

የሚከተሉት ከ 4-6 የሚደረሱ ሰዎች ለተግባራዊ ቡድኑ ምረጥ

*መሪ* ______________________________

ተተኪ *መሪ* ______________________________

አስተናጋጅ ______________________________

ሌሎች ክርስቲያኖች (ልምድ ያላቸው *መሪዎች*) ______________________________

አዲስ ክርስቲያን ወይም አማኝ ያልሆነ ሰው በጀማሪ ቡድንህ ውስጥ ጨምር ______________

***ማስታወሻ፡- ወርክሾኘ አሰልጣኙ፣ ከ4-6 ሰዎችን ያቀፈ ቡድኖችን አብጅ፤ እያንዳንዱ ቡድን የራሱን መሪ እንዲመረጥ አድርግ፡፡ የቡድኑ መሪ ለማጅ መሪና አስተናጋጅ ይምረጥ፡፡ ለተመረጡት መሪዎች በሚከተለው ኃላፊነቶች ላይ አስቀምጣቸውና የትንሹን ቡድን አጀንዳ ሲከተሉ በመደበኛው ሳምንታዊ የቡድን ጊዜዎች ላይ የሚሰሩትን ያህል እንዲሰማቸው አድርገህ ምራቸው፡፡ በአንድነት ጊዜያችሁን በደስታ አሳልፉ!***

### የትንሹ ቡድን አጀንዳ

# አቀባበል (15-20 *ደቂቃ*)

**አስተናጋጅ**

- *መቀመጫዎችን* በክብ ከአንድ ብቸኛ ባዶ ወንበር *ጋር* አዘጋጅ
- እያንዳንዱን ሰው በወንድማዊነት ሰላም በል፡፡
- በቀሪ *መቆጣጠሪያ* ቅጽ ላይ እያዳንዳቸው *መገኘታቸውን* አረጋግጥ

***መሪ***

- በፀሎት ኘሮግራሙን ጀምር ወይም ሌላ ሰው እንዲፀልይ አድርግ፡፡

**ለማጅ** (በመሰልጠን ላይ ያለ *መሪ*)

- የማካፈል ግዜውን ምራ
    - የማካፈል ጥያቄዎችን ተጠቀም፤ አንድ ጥያቄ በመምረጥ እያንዳንዱ ሰው እንዲመልስ ዕድሉን ስጣቸው - ወይም
    - ካለፈው ሳምንት ካጋጠማቸው መጥፎ ወይም ጥሩ ነገር ወይም ካሳለፉት ሁኔታ ተነስተው ሊያካፍሉ ይችላሉ፡፡
    - አንድ ወይም ሁለት ሰዎች አልፎ አልፎ የአንድ ደቂቃ ምስክርነታቸውን እንዲያካፍሉ አድርግ፡፡
    - ግልፅና እውነተኛ መሆንህን እርግጠኛ ሁን፡፡

# አምልኮ (15-20 *ደቂቃ*)

***መሪ***

- አንድ ወይም ሁለት የምስጋና መዝሙሮችን አዘምራቸው ወይም ለተመለሱ ፀሎቶች እግዚያብሔርን አመሰግን፡፡
    - በእግዚአብሔር ባህሪይ ላይ አተኩር
    - አስፈላጊ ከሆነ አልፎ አልፎ የፍቅር ግብዣ አድርጉ፡፡
    - እያንዳንዱን ሰው እንዲሳተፍ አበረታታው፡፡ በመደዳው በመፀለይ ማንንም እንዳታስደነግጥ ተጠንቀቅ

# ወንጌል ማካፈል (20-30 ደቂቃ)

**ተተኪ *መሪ*** (በመሰልጠን ላይ ያለ መሪ)

- በአንድ ለአንድ መልኩ መሰረታዊን፣ ደቀመዝሙር የማድረግን ወይም ማካፈልን የአገልግሎት ዕድገት መቆጣጠር።
- ሌሎችን ማለትም ደቀመዝሙር ሊሆኑ ወይም ሌሎችን ደቀመዝሙር ሊያደረጉ ያሉ ሰዎችን መለየት
- የወንጌል ስርጭት ስልትህን ትኩስ ማድረግ፤ እቅድ ማውጣት።
- በተፅዕኖ ክልልህ ለፀለይክላቸው ሰዎች የታየውን ለውጥ ሪፖርት ማድረግ።
- የፀሎት ጊዜውን መምራት። ባዶው ወንበር በአንድ ሰው እንዲያዝ ፀልይ። ንግግራዊ የፀሎት አይነትን ተለማመድ (ፀሎቶችህ በአጫጭር ዓረፍተ-ነገሮች ይገለፁ) የፀሎት ርእሶችን በፀሎትህ ውስጥ አካትት፤ በፀሎት ርእሶችህም ሆነ በሌላ ጉዳዮች ሰዎች እንዲሳተፉ አድርግ። ለጐረቤትህ ወይም ለጓደኛህ ወንጌሉን የመመስከር /የማካፈል ዕድል እንድታገኝ ፀልይ።
- **ብዙ ፀሎት - ብዙ ሐይል - ብዙ ምስጋና** በተሰኘው ገፅ ላይ የፀሎት ርዕሶችህንና መልሶቻቸውን መመዝገብ (ገፅ 24)

# የቃል ጊዜ (20-30 ደቂቃ)

***መሪ***

- የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናቱን ጊዜ ምራ፤ ለዛሬው ለምሳሌ የተቀመጠውን የህይወት ጥናት ትምህርት ተጠቀም አስታውስ ልትሰብክ ወይም ልታስተምር አይደለም የተቀመጥከው ነገር ግን በቡድኑ አባላት መካከል እየተደረገ ያለውን ውይይት ልታመቻች ነው።
- እያንዳንዱ የቡድን አባላት እንዲቀራረቡ አድርጋቸው - ማወቅ የሚገባቸውን አስተዋውቅ።
- እያንዳንዱ ሰው አማኝ ያልሆነ ወይም አዲስ ክርስቲያን ወደ ቡድኑ እንዲያወጣ አበረታታ። በተለይም እየሰለጠኑ ያሉትን።
- በፀሎት ቡድኑን አሰናብት።

## *ሁልግዜ በሰዓቱ ጀምርና ጨርስ!*

**አስተናጋጅ**

- መነቃቂያ / መዝናኛ (እንደ አማራጭ) የቡድኑ ጊዜ ካበቃ በኂላ ማገልገል፣ ምክንያቱም የሚሄዱ ሰዎች ካሉ መሄድ እንዲችሉ ነው። ለማዝናናት ለማገልገል ከፈለግህ/ሽ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግሽን/ህን እርግጠኛ ሁን/ኚ።

**ዛሬ ከመሄዳችሁ በፊት ከታች የሚገኘውን የዕቅድ ወረቀት ሙሉ!**

*መሪዎች ወይም መጋቢያን በሚከተለው የዕቅድና የውይይት ጊዜ ይምሩ።*

☐ 1. በጀማሪ ቡድኑ ውስጥ ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆኑትን ሰዎች አግኝና ከተቻለ በዋናው ቡድን ውስጥ አስገባቸው።

**እያንዳንዱ ቡድን**

☐ 2. የራሳችሁን የህይወት ቡድን መሪ ምረጡ። ________________________________

☐ 3. የራሳችሁን ተተኪ መሪ ምረጡ ________________________________

☐ 4. የራሳችሁን የመስተንግዶ አገልጋይ ምረጡ ________________________________

☐ 5. የምትገናኙበትን ቀን __________ የሚጀመረበት ቀን __________

የመጀመሪያ ሰዓት __________ የሚያልቅበት ሰዓት__________ ምረጡ ።

☐ 6. የቤት ለቤት አገልግሎትህ ቡድን ስም አውጣ፤ በገፅ 18 ላይ ***በስም ውስጥ ምን አለ*** የሚለውን ተመልከቱ።

☐ 7.ለመፅሀፍ ቅዱስ ጥናታችሁ ስርአተ ትምህርት ምረጡ። ከህይወት ጥናቶች ትምህርቶች ልትጀምሩ ትችላላችሁ።www.dynamicchuches.org የተሰኘውን መረጃ መረብ በማየት ሌሎች መርጃ መጽሐፍቶችን ልትመርጡ ትችላላችሁ።

☐ 8.**የሕይወት ቡድን *መሪው* ከተተኪ *መሪው ጋር ለመምራት መማር- የተተኪ መሪ ስልጠና*** ክፍለ ጊዜዎችን ለመከታተል (በወር አንድ ጊዜ ለአንድ ሰዓት) እና ***ዳይናሚክ ማካፈልን*** ለመከታተል (በወር አንድ ጊዜ ለሁለት ሰዓት) ጊዜ አመቻቹ።

***ለመምራት መማር*** ክፍለ ጊዜዎች፡- ቀን________ ሰዓት________ ቦታ____________

***ለዳይናሚክ ማካፈልን*** ክፍለ ጊዜዎች፡- ቀን________ ሰዓት________ ቦታ____________

*በህይወት ቡድኑ መጀመር የተሰማችሁን ደስታ አካፍሉ፤ ለእያንዳንዱም ሰው ያላችሁን አድናቆት ግለፁ።*

*በፀሎት ዝጉት።*

# የህይወት ቡድን

## ሳምንታዊ መቆጣጠሪያ ቅጽ

| ሙሉ ስም ባል/ሚስት | ቀን | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |

# የማካፈል ጥያቄዎች

1. በህይወትህ ደስ ስለተሰኘህባቸው ቀናቶች አካፍል፡፡
2. ራስህን አንተን ለማያውቅህ አንድ ሰው እንዴት ነው የምታስተዋውቀው /የምትገልፀው?
3. በዛሬው ቀን ያለህበትን ስሜት የሚገልፀው የትኛው የቀለም አይነት ነው?
4. ከቅርብ ጓደኛህ በጣም የምታደንቀው ምንድን ነው?
5. እግዚአብሔር አንተን የተናገረበት ለየት ያለ መንገድ ምንድን ነው?
6. እስከዛሬ ካነበብካቸው መፃህፍት ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ነው? ለምን?
7. ስትሞት በቀብርህ ድንጋይ ላይ ፅሁፍ እንዲፃፍ ብትፈልግ፣ ምን ተብሎ እንዲፃፍ ትፈልጋለህ?
8. እቤት ውስጥ መስራት የምትወደው አንድ ነገር ምንድን ነው?
9. ከተቀበልካቸው ስጦታዎች የተመረጠው የቱ ነው? ለምን?
10. በህይወትህ መለወጥ የምትፈልገው አንድ ነገር ቢኖር ምንድን ነው?
11. እግዚአብሔር ላንተ ከቃል ያለፈ ሆኖ ያገኘህበት አጋጣሚ ከነበረ መቼ ነው?
12. በአስራሁለት ዓመትህ የት ትኖር እንደነበረና ስለምታስታውሰው አንድ ነገር አካፍል፡፡
13. ልጅ እያለህ በጣም የምትወደው የጫወታ አይነት ምን ነበር?
14. በጣም ውድ ከሆነ ንብረቶችህ ሁለቱ ወይም ሶስቱ የትኞቹ ናቸው? ለምንድነው ውድ የሆኑት?
15. በፊት ለፊትህ ባለው ዘመን ልታየው የምትፈልገው አንድ ነገር ምንድን ነው?
16. በግል ግንኙነትህ ልታሻሽለው የምትፈልገው አንድ ነገር ምንድን ነው?
17. መቼ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ኢየሱስ የሰማኸው? ስለእርሱስ ምን አሰብክ?
18. በአየር ንብረት ገለፃ መሰረት ህይወትህን ግለፅ?
19. ከፍተኛ እርካታ የሚሰጥህ አንድ ነገር ምንድን ነው?
20. በጣም የሚያስፈራ ጊዜ ____________________________
21. ወደ _________________________ መጓዝ እወዳለሁ፡፡
22. በትርፍ ጊዜህ ምን መስራት ትወዳለህ?
23. በቤተህ ውሰጥ የትኛውን ስፍራ ነው በጣም የምትወደው?
24. ልጅ እያለህ በተለየ ሁኔታ የምተወደው አጫዋች የቤት እንስሳ ነበረህ? ለምን ልዩ ሆነ?
25. በሚቀጥለው ዓመት በዚህ ጊዜ በሙያህ ልታየው የምትወደው መሻሻል ምንድን ነው?
26. ከክርስቶስ ቀጥሎ በህይወት ተፅዕኖ ያደረገብህ ሰው ማን ነው? ለምን?
27. ልጅ እያለህ የቅርብ ጓደኛህ ማን ነበር? ለምን?
28. __________________________ መማር አላቋርጥም፡፡
29. የሚመጣው ዓመት ለኔ ጥሩ ይሆናል ምክንያቱም ____________________________
30. እኔ _________________________ መሆኔን በማወቃቸው ሰዎች ሊገረሙ ይችላሉ፡፡
31. በቀኑ ወይም በሳምንቱ መጨረሻ በኋላ ከውጥረት ለመርገብ ወይም ትንሽ ተንፈስ ለማለት ምንድነው የምታደርገው?
32. ምንድነው የሚያስጨንቅህ?
33. በጣም በተለየ ሁኔታ የምትወደው ሽታ የቱ ነው? ከእርሱስ ጋር ምን ትዝታ አለህ?

ብዙ ጸሎት

ብዙ ኃይል

ብዙ ምስጋና

| የፀሎት ጥቃቂዎች/አርዕስት | ቀን | መልስ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# የህይወት ጥናቶች

## የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት መጠራት

## ሉቃ 5-1-11

በገፅ 23 ላይ የሚገኘውን የማካፈል ጥቃቄዎች ተጠቀም ወይም የሚከተሉት ጥቃቄዎች መልስ ፣እያንዳንዱ ሰው አንድ ጥያቄ መርጦ ማካፈል ያስፈልገዋል፡፡ በህይወት ለመጀመሪያ ግዜ ምን ተሰማህ፡፡

1. ዋና ለመዋኘት ስትሞክር ምን ተሰማህ
2. አዲስ የሆነ ስፖርት ስትሞክር
3. ከክፍል ወደ ክፍል ስትዘዋወር
4. ከቤት ስትወጣ
5. ስራ ስታገኝ

=====================================================

**የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል ግንኙነት**

ሉቃስ 5÷1-11 አንብብና የሚከተሉትን ጥቃቄዎችና መልሶች አንብብ፤ ከብዙ ሰዎች ጋር በመሆን የመረጥከው መልስ ለምን ያንተ መልስ እንደሆነ አካፍል፡፡

1. ኢየሱስ ጀልባ በፈለገ ግዜ ስምዖን ጴጥሮስ መረቡን ያጥብ የነበረው በአጋጣሚ እንደሆነ ታስባለህ ወይስ ያ የእግዜአብሔር ዕቅድ ነበር?
ሀ/ በአጋጣሚ ነበር
ለ/ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ነበር
ሐ/ እርግጠኛ አይደለሁም
2. አንተ ስምኦን ጴጥሮስን ሆነህ ቢሆን ኖሮ ጌታ ኢየሱስ እርሱን «ወደ ጥልቁ ፈቀቅ ብለህ መረብህን ጣል» ባለው ጊዜ ምላሽህ ምን ይሆን ነበር?
ሀ/ እንደ ጴጥሮስ ይሆን ነበር
ለ/ ባለማድረግ ምክንያቶችን አስቀምጥ ነበር
ሐ/ ኢየሱስ ስብከቱ እንዲቀጥልና እኔም አሳ ማጥመጄን እሰራ ነበር
መ/ አሳዎቹ በሚከማቹበት ግዜ እጠቁመው ነበር፡፡
ሠ/ ዝም ብዬ እሄድ ነበር፡፡
3. መረባቸው እስኪቀደድ ድረስ በጣም ብዙ አሳ በያዙ ጊዜ፣ ስምኦን ጴጥሮሰ ምን ያስብ እንደነበር ምን ትገምታለህ?
ሀ/ ከዚህ ሁሉ አሳ ሽያጭ የሚያገኘውን ገንዘብ
ለ/ ኢየሱስን መጠራጠሩ ትክክል እንዳልነበር
ሐ/ ምን እንደሚያስብ አያውቅም ነበር
መ/ ኢየሱስ ማን እንደሆነ አረጋግጦ ነበር
4. ስምኦን ጴጥሮስ «ጌታ ሆይ ከእኔ ራቅ እኔ ኃጢያተኛ ነኝ» ማለቱ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
ሀ/ እኔ ትሁት ነኝ ምክንያቱም ስለማጥመድ ከእኔ ይልቅ አንተ ታውቃለህ፡፡
ለ/ በኃጥያት የተበከለ ህይወት ስላለኝ ያንተ በአጠገቤ መሆን ጥሩ ስሜት / ነፃነት እንዲሰማኝ አያደረገኝም
ሐ/ አንተ እንደ ቃልህ እንደሆንክ አውቃአለሁ ነገር ግን አንተን ለመከተል ዝግጁ አይደለሁም፡፡
መ/ እኔን የበደለኝነት ስሜት እንዲሰማኝ ማድረግህን ተው፡፡
ሠ/ ግራ ተጋብቻለሁ አንተን መከተል እፈልጋለሁ ነገር ግን እሺ ካልኩ በህይወቴ የተወሰነ ለውጥ ማድረግ እንደሆነስለማውቅ እፈራለሁ፡፡

=====================================================

**ማዛመድ**

የአንተን የመንፈሳዊ ህይወት ጉዞ ተመልከት

1. እንዴት ነው ያንተ መንፈሳዊ ህይወት ጅማሬና የስምኦን ጴጥሮስ የሚነፃፀረው?
ሀ/ በቅፅበት እንዳለመሆኑ
ለ/ በዕውቀት ስለመሆኑ
ሐ/ እንደ ግራመጋባት
መ/ በቅፅበት በመሆኑ
ረ/ እርግጠህኛ አይደለሁም
ሠ/ በልዩ ሁኔታ ነገር ግን ልክ እንደ እውነት
2. የአንተን መንፈሳዊ ጀልባ ሁኔታ እንዴት ነው የምትገልፀው?
ሀ/ እየሰመጠ ነው
ለ/ ተረጋግቶ (ፀንቶ) ነው ያለው፡፡
ሐ/ በትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እየሄደ ነው
መ/ ጥገና ያስፈልገዋል
ረ/ በወጀቡ እየተናጠ ነው፡፡
ሠ/ በትክክለኛ ሁኔታ እየሄደ ነው
3. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ወደ ጥልቁ ውሃ ፈቀቅ በልና አሳ ለመያዝ መረብህን ጣል» ብሎ ቢጠይቅህ መልስህ ምን ይሆን ነበር?
ሀ/ እፈራ ነበር
ለ/ የማይረባ እንደሆነ እገምት ነበር
ሐ/ እሺ ነገር ግን....
መ/ ሌላ ሰው አብሮኝ ቢሆን አደርገዋለሁ
ሠ/ መልካም መቼ እንጀምር
ረ/ ምን እያልክ እንዳለህ አልገባኝም
4. እንድትሄድ የሚያደርግህ ነገር ምንድን ነው?
ሀ/ ትርፍህን ለማስላት የምትወስደው ጊዜ
ለ/ ለመዘጋጀት የምትወስደው ጊዜ
ሐ/ እርግጠኛ አይደለሁም
መ/ ከጓደኞቼ የማገኘው ድጋፍ
ረ/ መታዘዝ
ሠ/ ህይወቴን ለማስተካከል የሚያስፈልገኝ እርዳታ

# ለቡድንህ ስርዓተ ትምህርት ማዘጋጀት

የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናቱን በምትመርጥበት ጊዜ ዋናው ትኩረት ከህይወት ጋር ተዛማችነት ባላቸው ርዕስ ጉዳዩች ላይ መሆኑ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም የቤተክርስትያን አባላት ሁለት መንታ መንገዶች ላይ ነው ያሉት፤ ለመቀበል የተዘጋጀ አስተሳሰብና (አመለካከትና) ተጨማሪ ብዙ ዕወቀትን የሚፈልግና በትንሹ የሚሰጥ፣ ለክርስቶስ ለመኖርና በሌሎች ላይ የራስን ህይወት መዋዕለ ነዋይ ለማድረግ ትንሽ መታዘዝ ያለው አመለካከት ነው፡፡ ለዚህ ነው መፅሀፍ ቅዱስ ጥናቱ የግድ ከህይወት ጋር ተዛምዶ ግባቸው በመታዘዝና በተግባራዊ ህይወት ላይ ማተኮር ያለበት፡፡

**ስርዐተ ትምህርቱን በምታዘጋጅበት ግዜ ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገቡ ጥያቄዎች**

- የቡድናችን ዓላማ ምንድን ነው?
- በዚህ ጊዜ ቡድናችን በጣም የሚያስፈልገው ምንድን ነው?
- ቡድናችን የመንፈሳዊ ዕድገቱ ምን ያህል ነው?
- ከቤተክርስቲያናቱ የትኩረት አቅጣጫ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
- ከ 20-30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ የሚያልቅ ነው?

ስርዐተ ትምህርቱ ከመጋቢው የየጊዜው መልዕክት ውስጥ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ በአምልኮ ጊዜ መጋቢው የመልዕክቱን ዋና ዋና ክፍል በወረቀት አዘጋጅቶ እያንዳንዱ ሰው የሚያገኝበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይችላል፡፡ በተጨማሪም እርሱ ወይም ሌላ ሰው በትንንሽ ቡድኖች ውስጥ የሚያገለግሉ ተግባራዊ ህይወት የሚመሩ ጥያቄዎች ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም መሪዎች ጥያቄዎችን በማዘጋጀቱ ሂደት ሊያግዙ ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱንም የቡድን አባል ለተግባራዊ ህይወት ዘይቤ ለተለወጠና ክርስቶስን ማዕከል ላደረገ ህይወት ሊያበረታታቸው ይገባል፡፡

ስርዐተ ትምህርቱ በቡድኑ ውስጥ ግንኙነትና ጓደኝነትን የሚፈጥር መሆኑን አረጋግጥ፡፡ አምስት ወይም ስድስት ጥያቄዎች ከህይወት ተዛምዶ ጋር በመሆን በቂ ናቸው፡፡ ምን? ከሚሉ የጥቃቄዎች ይልቅ ለምን? የሚሉ ጥቃቄዎችን ቢይዙ ጥሩ ነው፡፡

አማራጭ ስርዐተ ትምህርቱ በተወሰነ ርዕስ ላይ የተመረኮዙ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናቶች ወይም ለህይወት ቡድኑ በተለየ ሁኔታ ጥናቶችን ማዘጋጀት ይችላል፡፡ ልክ እንደ ዳይናሚክ ቸርች ኢንተርናሽናል የህይወት ጥናቶች (በገፅ 25 የሚገኘውን ነውና ተመልከት)

ብዙዎቹ የቡድኑ አባላት በአንድ ለአንድ ስልጠና ከደቀመዝሙራቸው ወይም ከደቀመዝሙር አድራጊያቸው ጋር ተጠምደው እንዳለ አስታውስ፡፡ ስለሆነም ምንም አይነት የቤት ስራ ዝግጅት ከቡድኑ ግንኙነት በፊት ሊኖር አይገባም፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ሁኔታ፣ ምናልባት አንድን ሰው ሳያጠናቅቅ ከመጣ ተስፋ ሊያስቆርጠውና ከቡድኑ ሊቀር ይችላል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ትምህርት በራሱ የቆመ ቢሆን ተገቢ ነው፡፡ ከባለፈው ትምህርት ጋር የግድ የሚቀጥል መሆን የለበትም፤ ምክንያቱም ለአንድ ለአዲስ ሰው በተከታታይ ጥናቶች ከመሃል መጀመሩ በጣም ከባድ ሊሆንበት ይችላል፡፡

> በዚህ መፅሀፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ***የህይወት ቡድኑ መሪ ቃል መግቢያ ቅፅ*** ለህይወት መሪነት ባመለከቱ መሪዎች መሞላት ይኖርበታል ***የምስክር ወረቀቱም*** ለአሰልጣኙ ተሞልቶና ይህንን ስልጠና በወሰዱት ሰልጣኞች በሙሉ መፈረም ይኖርበታል፡፡

# የዳይናሚክ ማካፈል ወርክሾኘ (2 ሰዓት)

***ማስታወሻ፡- እያንዳንዱ ተሳታፊ የዳይናሚክ ማካፈል ወርክሾኘ ለመውሰድ ከመምጣቱ በፊት የዳይናሚክ ማካፈል መፅሀፍ ሊደርሰውና የዚህን መፅሀፍ ትምህርት አንድ አጠናቅቆ መገኘት ይኖርበታል። ከስብሰባው በፊት አንድ ትምህርት ማጠናቀቅም የሚጠበቅ ነገር ነው።***

- በፀሎት ኘሮግራሙን ጀምር
- በርካታ ሰዎች በማግኘት በዳይናሚክ መሰረታዊና በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ያገኙትን ተሞክሮ ያካፍሉ።
- እያንዳንዱ ሰው የዳይናሚክ ማካፈል መፅሀፍ ለሰልጣኙ ጠቅላላ መመሪያው ጋር እንደያዙ አረጋግጥ። ይህም ከዳይናሚክ ማካፈል መጨረሻ እንደሚገኝ ጠቁማቸው።
- ጠቅላላ መምሪያውን ያለ ማብራሪያ ዝም ብለህ አንብበው (አንዳንዶቹ መመሪያዎች ከዳይናሚክ ማሰልጠኛ ጋር ተመሳሳይ ናቸው።)
- እያንዳንዱ ሰው የዳይናሚክ ማካፈልን ትምህርት አንድ ማጠናቀቅ ይኖርበታል። (ምናልባት ተሳታፊዎቹ ትምህረት አንድን ያላጠናቀቁ ከሆነ ተጨማሪ ሰዓት ወስደው በግላቸው በዚህ ጊዜ እንዲሰሩ ማድረግ) ከዛም ይቀጥሉ።
- ትምህርት አንድን ለመስራት በጥንድ ይቀመጡ። የትምህርት አንድ ማረጋገጫውን ተመልከት።
- በክፍሉ ውስጥ ለማየት በምትመላለስበት ጊዜ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ የተገኘህ ሁን።
- እንደገና በአንድነት እንዲሆኑ አድርጋቸው። ለጥያቄ እድል ስጥ።
- አንዱን ፈቃደኛ ከሆነ የአንድ ደቂቃ ምስክርነቱን እንዲያካፍል ጠይቅ። ጊዜው እስከፈቀደ ድረስ በርካታ ሰዎች የራሳቸውን ምስክርነት ያካፍሉ።
- ምስክርነታቸውን እያካፈሉ ያሉትን ሰዎች ማበረታታትና ማገዝህን አረጋግጥ።
- እያንዳንዱ ሰው ምስክርነቱን ካካፈለ በኋላ ቡድኑ የእርሱን / የእርሷን የከዚህ በፊትና በኋላ ምስክርነት እንዴት እንደነበረ ለይተው እንዲናገሩ ጠይቅ። በተረጋጋ ሁኔታ አስተያየት ስጥ፤ ማንንም እንዳታስደነግጥ ተጠንቀቅ።
- ከእረፍቱ በኋላ ለቤት ለቤት ጉብኝቱ ማሳያ የሚሆንህን ሰው ለመምረጥ ተመልከት

## የዕረፍት ጊዜ (15 ደቂቃ)

በዕረፍት ጊዜው ለቤት ለቤት ጉብኝቱ ማሳያ ተዘጋጅ።

- በማሳያው ላይ ሊካተቱ የምትፈልጋቸው ሰዎች ማዘጋጀትህን አረጋግጥ።
- ለሰርቶማሳያው ከአንተ ጋር ለጉብኘት አብሮ የሚሄድን አንድ ሰው ምረጥ (ምናልባትም ጥሩ የአንድ ደቂቃ ምስክርነት የሰጠው ሰው ሊሆን ይችላል) ያንተ አጋር እንዲሆን ጠይቀው። በምትጠራው ጊዜ እንዲመለከትህና ምስክርነቱን እንዲያካፍል ንገረው።
- ከቡድኑ አንድ ጥንዶች ምረጥና የሚጎበኙ ጥንዶችን መስለው እንዲጫወቱ አድርግ
- የምትጎበኛቸው ሰዎች በወንጌል የማያምኑ ከሆኑና ለወንጌሉ ልባቸው በመክፈት ክርስቶስን ለመቀበል ፍቃደኛ ከሆኑ፣ እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ምራቸው። ***በወንጌሉ መመስከሪያ በስተግራ ካለው ክበብ ውስጥ በመጠቆም (ክርስቶስ ከህይወታቸው ክበብ ውጪ) እንደሆነ ንገራቸው። ነገር ግን በስተቀኝ ባለው ክበብ ውስጥ እንዲሆኑ ከፈለጉና ጌታን ለመቀበል ከፈለጉ አንተ የምትፀልየውን ፀሎት በፍቃደኝነት መፀለይ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም*** ***በህይወት ቡድኑ*** ***ውስጥ ለመሳተፍ ፍቃደኛ መሆንና*** ***የዳይናሚክ መሰረታዊ*** ***ትምህርትን ለመውሰድ ፍቃደኛ መሆን ይኖርባቸዋል።*** *(ለአንተ አስቸጋሪ እንዳይሆኑ ንገራቸው! አዎንታዊ ተሞክሮ አድርገው!)*
- አንድ ጠረጴዛ ከ 4 ወንበሮች ጋር አሰናዳ። (ማንኛቸውም ጀርባቸው ወደ ህዝቡ መሆን የለባቸውም)

## የጉብኝት ሰርቶ ማሳያውን ጀምር (30 ደቂቃ)

- ለሁሉም ቡድን ***በዳይናሚክ ማካፈል*** **ክፍል ሶስት** ውስጥ እንዳለው **ከሐ. የመዳረሻ ቅደም ተከተል** ተነስተህ ምን ልታደርግ እንደሆነ እና በጉብኝትህ ጊዜም እንዲከታተሉ ግለፅላቸው።
- ***እግዚአብሔርን በግልህ ለማወቅ ትፈልጋለህ?*** የሚለውን ወይም ***ስለ አራቱ መንፈሳዊ ህጎች ሰምተሃል?*** የሚሉት ትንንሽ የወንጌል መመስከሪያ መጽሐፍቶች ለእያንዳንዳቸው አድል። በሰርቶ ማሳያው ጉብኝት **ለጥንዶቹ መፅሀፍቶቹን ስታነብ** እነርሱ ከአንተ ጋር **ይከተሉ**።
- **የአንተን አጋር** እና **ጥንዶቹን** አስተዋውቅ።
- ሁለቱ ጥንዶች በመካከል ባሉት ሁለት ወንበሮች እንዲቀመጡ አድርግ።
- አንተና አጋርህ ከውጪ እንደሚመጣና በር ላይ ቆሞ እንደሚያንኳኳ ሰው ለመሆን አስመስሉ። ወደ ውስጥ እንድትገቡና እንደትቀመጡ ይፈቅድላችኂል። ወንጌሉን ልታካፍለው በምትፈልገው ሰው አጠገብ መቀመጥ ይኖርብሃል።
- ልክ ***በዳይናሚክ ማካፈል*** ጉብኝት ፎርም ትምህርት ሦስት እንድትገልፀው፣ **ከሐ. የመዳረሻ ቅደም ተከተልን** ተከተል።

***ማስታወሻ፦ ያለምንም ማብራሪያ መፅሀፍቶቹን ብቻ አንብብ። የአንተን ይህንን አሰራር በትክክለኛ ሁኔታ ምሳሌ መሆን በጣም የሚጠቅም ጉዳይ ነው።***

- ከሰርቶማሳያው በኂላ ተሳታፊዎችን አመሰግን።
- በዳይናሚክ ማካፈል ወይም ጉብኝት ላይ ጥያቄ ካላቸው እድል ስጥ።
- በዚህ ሳምንት እያንዳንዱ ሰው ለአንድ ሰው የወንጌል መፅሀፍቶቹን እንዲያካፍል አበረታታ። በጣም ቀላል እንደሆነና ትልቅ ዋጋ እንዳለው አሳስባቸው።
- መሪዎች ተለማማጆችን በዳይናሚክ ማካፈል እንዲያሰለጥኑ ግለፅላቸው። ነገር ግን እያነዳንዱ ሰው ለመሰልጠን ይበረታታል።
- እንደገና ቡድኑን በአንድነት ሰብሰቦ ዳይናሚክን ማካፈልን ማን ማንን እንደሚያሰለጥን ወስን።
  ከወርክሾፑ በኂላ ______________ ______________ ን ያሰለጥናል።
  ከወርክሾፑ በኂላ ______________ ______________ ን ያሰለጥናል።
  ከወርክሾፑ በኂላ ______________ ______________ ን ያሰለጥናል።
- የትምህርት ሁለት የመዘጋጃ ስራ አውጥተህ ተመልከት፤ ትምህርት ሁለት ከአጋራቸው ጋር በሚቀጥለው ጊዜ ከመገናኘታቸው በፊት መጠናቀቅ ይኖርበታል። (ምናልባት ትምህርት አንድን በመጀመሪያ ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል)።
- ከወርክሾፕ ስልጠና በኂላ የተቀሩትን ትምህርቶች ይጨርሱ ዘንድና የሚገናኙበትን ቀኑንና ጊዜውን እንዲያመቻቹ እድሉን ስጣቸው። ልክ እንደ ዳይናሚክ መሰረታዊ እያንዳንዱ ሰው አንድ ሰው በመፈለግ ከዳይናማክ ማሰልጠኛ ትምህርት አንድ በመጀመር ማሰልጠን ይኖርበታል። የተቀሩትን ትምህርቶች ለማጠናቀቅ ከተጓዳኞቻቸው ጋር ይስሩ።
- ምናልባት ሌላ የዳይናሚክ ማሰልጠኛ ወርክሾፕ ለማድረግ እቅድ ካለህ

ቀን ________ሰዓት ____________________ ቦታ ________________________ ወስን።

- ከተጓዳኞቻቸው ጋር በፀሎት እንዲሆኑ ካደረግህ በኂላ በፀሎት ኘሮግራሙን ዝጋው።

# ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን የማስፋፊያ ወርክሾፕ

**ክለሳ፡-**

# እግዚያብሔር ለቤተክርስቲያን ያለው አላማ ምንድን ነው?

***ታላቁ ተልዕኮ***

***«ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወለድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው፤ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤እኔም እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ ሁልግዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።»***

(ማቴ 28-18-20)

**ታላቁ ተልዕኮ «ህዝቦችን ሁሉ - - - - *ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው*» ይላል።**


***ደቀመዝሙር ማነው?***

ክርስቶስን ተቀብሎ በክርስቶስ ትምህረት የሚኖር ነው።

***እንዴት ደቀመዝሙር ማድረግ እንችላለን?***

የእኛ ደቀመዝሙር መሆን ሌሎችን ደቀመዝሙር ለማድረግ ግድ ነው።


- **በመሄድ --- ወንጌል ስርጭት**
- **በማጥመቅ** --- ከክርስቶስ ሞት፣መቀበርና መነሳት ጋር **መመሳሰል**
- **እንዲጠብቁ በማስተማር --- ደቀመዝሙርነት።**




# ደቀመዛሙርት ማድረግ የቤተክርስቲያን ልብ ነው። ምክንያቱም እርሱ የታላቁ ተልዕኮ ልብ ስለሆነ።

# ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት

በመንፈሳዊ ቤተሰብ ውስጥ ማደግ ከተፈለገ ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን ማጕልበት ወሳኝ ነው። የታላቁ ተልዕኮን ዕውን ለማድረግ ይረዳን ዘንድ መጕልበት የሚገባውን የመፅሀፍ ቅዱስ መርህዎችን ያካተተ ሂደት።




## ለታላቁ ተልዕኮ ዕውን መሆን ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወሳኝ ነው

# የምትጨምረዋና እራሷን የምታባዛዋ ቤተክርስቲያን

(ይህ በ30ና ከዛ በላይ በሆነ ሰዎች የሚሰራ ነው)

1. በቡድኑ ፊት ሁለት ሰዎች እንዲወጡ አድርግ፡፡ አንደኛው መጋቢ "ሀ" ሌላኛው ደግሞ መጋቢ "ለ" ሆነው ይጫወታሉ፡፡

2. ለቡድኑ ሁለቱም መጋቢያን እኩል ችሎታና እኩል መጠን ያላቸው ቤተክርስቲያን እንደሚመሩ ግለፅላቸው፡፡ መጋቢ "ሀ" የደቀመዝሙር የማድረግ ያለውን የመባዛት አቅም ያልተገነዘበ/ያልተረዳ/ ነው፡፡ ስለሆነም ቤተክርስቲያኑ በመጨመር እንድታድግ ይፈልጋል፡፡ መጋቢ "ለ" ደቀመዛሙርትን በማሳደግ በሚመጣው መባዛት የሚገኘውን ዕድገት ተረድቷል፡፡

3. ከመጋቢ "ሀ" ጋር በመሆን አሳያቸው፡፡ ወደ ጆሮው በመጠጋት በሹክሹክታ ፐስ በለው(ይህ ወንጌሉን በእርሱ መመስከርህንና እርሱ ክርስቶስን መቀበሉን ይወክላል) ከዚህ በኋላ መጋቢ "ሀ" ወደ ጉባኤው በመሄድ ተመሳሳይ በሆነ አካሄድ በሌላ ሰው ጆሮ ላይ እያንሾካሾከ ወደፊት ለፊት ያመጣል፡፡ መጋቢ "ሀ" በተደጋጋሚ በመመላለስ ይሄኑኑ ተግባሩን በማድረግ በጉባኤው ያሉትን ሁሉ ወንድና ሴት ወደ ፊት ለፊት እያመጣ እዛው ይተዋቸዋል፡፡

4. ከመጋቢ ለ ጋር በመሆን አሳይ፡፡ ከሚከተሉት ተጨማሪ ስራዎች ባሻገር ከላይ በተራ ቁጥር 3 እንደተቀመጠው ያደርጋል፡፡ ሰዎቹን ወደ ፊት በሚያመጣበት ጊዜ ለሁለተኛ ግዜ ወደጆሮአቸው ተጠግቶ ያንሾካሹካል (ይህ እነርሱን ደቀመዝሙር ማድረጉን ይወክላል)፡፡ ከዛ በኋላ ከአዲሱ ደቀመዝሙር ጋር በመሆን እንደገና ወደ ጉባኤው ውስጥ ይገባሉ፡፡ ሁለቱም ሰዎችን ወደክርስቶስ እንደሚመሩና (የመጀመሪያው ፐስ) ሰዎችን ደቀመዝሙር እንደሚያደርጉ (2ኛው ፐስ) በመሆን እየተጫወቱ ሰዎችን ወደ ፊት በማምጣት እንደገና እያንዳንዱን ሰው በድጋሚ ሌሎችን እንዲደርሱ በማድረግ ጉባኤውን ሁሉ ይደርሳሉ፡፡

5. እያንዳንዱ መጋቢ መመሪያውን እንደተረዳ ማረጋገጥህንና በፍጥነት ነገርግን በጥንቃቄ እንዲንቀሳቀሱ አረጋግጥ፡፡ ከዛ በኋላ እነዚህን ወንጌል የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች እንዲደርሱ ላካቸው /ልቀቃቸው/፡፡

6. ለመጀመሪያ ግዜ የሁለቱም ቤተክርስቲያን በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያድጉ ይመስላሉ ነገር ግን የመጋቢ "ለ" ቤተክርስቲያን የመባዛት መርህን ስለተከተለች ወዲያው በፍጥነት ታድጋለች፡፡

7. ጉባኤው ሁሉ እንደተደረሰ «በየትኛው ቤተክርስቲያን መታቀፍ ትፈልጋላችሁ»? ብለህ ጠይቃቸው፡፡ በመጋቢ "ሀ" ቤተክርስቲያን ያሉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ወደ መጋቢ "ለ" ቤተክርስቲያን ለመቀየር መፈለጋቸውን ልብ በል፡፡

8. ቤተክርስቲያናቸው በፈጣን ዕድት ደቀመዝሙር የምታደርግ ቤተክርስቲያን እንደሆነችና የተገነባችውም መንፈሳዊ መባዛትን በሚያሳኩት መንፈሳዊ መራባት ላይ እንደሆነ ግለፅላቸው፡፡ ሁልግዜ ሌሎችን ደቀመዝሙር የሚያደርጉ ደቀመዛሙረትን ማፍራት መቀጠል ያስፈልገናል፡፡

# የግለሰቡ ሚና ደቀመዝሙር ለማድረግ ሂደት

የፈጣን እድት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት በቅደም ተከተል አንድን አዲስ ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ፍፁም ሙላት እንዲያድግ ለመረዳት የተዘጋጀ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆኑ ባህርይ ስላለው ለየት ያለ ፍላጐት በሚፈልግበት ጊዜ ለመድረስ የመንገዱ አመቺ መሆን ወሳኝ ነው፡፡ **የአንድ ለአንድ ደቀመዝሙር የማድረጊያ** ጊዜና **የትንሽ ቡድን** ግዜ እነዚህ ሁለቱን ወሳኝ ክፍሎችን ይገልፃሉ፡፡

# የአንድ ለአንድ ደቀመዝሙር ማድረግ

እያንዳንዱ ሰው በተለያየ የህይወት እድገት ደረጃ ላይ ነው ያለው፡፡ ለእያንዳንዱ ሰውም እኩል የማደጊያ ጊዜ ይሰጣል፡፡ የአንድ ለአንድ ስልጠና የግለሰቦችን ፍላጐት ለማሟላት በጣም አመርቂ የግላዊ ዕድገት ስርዓት ነው፡፡ በቡድኑ ውስጥ የአንድ ሰው ፍላጐት በሌላው ሰው ይሞላል፡፡ እንደሚመቻቸው ከቡድኑ ስዓት ውጪ በሚያደርጉት የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናትና ልምምድ፡፡

***በዳይናሚክ መሰረታዊ*** - አንድ አዲስ ክርስቲያንን ለመመስረት እንዲረዱ የተዘጋጁ 4 ትምህርቶች

***በዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግ*** - በክርስትና ህይወት በቀጣይነት ለማደግ የተዘጋጁ 9 ትምህርቶች

***በዳይናሚክ ማካፈል*** - እምነታቸውን ለሌሎች ለማስተላለፍ እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው ለመማር ለሚፈልጉ የተዘጋጁ 6 ትምህርቶች

### *እያንዳንዱ ደረጃ የአንድ ለአንድ አገልግሎት ከፍተኛ ደረጃ መስጠትን ይጠይቃል*

### የአንድ ለአንድ ስልጠና ለማደግ ፍላጐቱ ላላቸው ሁሉ ይገኛል፡፡

## የአንድ ለአንድ ግንኙነት ጥራት ያላቸው ደቀመዛሙርትን እና መሪዎችን ለማፍራት ጥሩ አውድን ያስገኛል

## ትንሹ ቡድን

የህይወት ቡድን የፍቅርና እንክብካቤ ቦታ ሆኖ እያንዳንዱ ሰው ጤናማ ዕድገት እንዲያመጣ የተዘጋጀ ነው፡፡ ለአዳዲስ ሰዎች አመቺና ተስማሚ የሆነ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ የቡድን አባላት ቀላልና ተወዳጁ ስፍራ የሆነና ጓደኞቻቸውን ወደ ቡድን ለመጋበዝ በሚያመች መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡


## የትንሹ ቡድን ጊዜ አውድ

1. አቀባበል/ማካፈል
2. አምልኮ/ፀሎት
3. የወንጌል ስርጭት/ፀሎት
4. የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ከማዛመድ ጋር
5. ስራ - የአንድ ለአንድ ደቀመዝሙርነት እና የመሪ መጐልበት

## የህይወት ቡድን የሚያጠቃልላቸው፡

1. መሪ
2. አሰተናጋጅ
3. አዲስ ክርስቲያን
4. ቤተክርስቲያን ጉቡኚዎች
5. ተተኪ መሪ
6. ከየትኛው የዕድገት ደረጃ ያሉ ፈቃደኛ የሆኑ ክርስቲያኖች
7. ተጋባዠ ወይም ከላይ የተቀመጡት ሰዎች ጓደኞች
8. ባዶ ወንበር አዲስ ለሚመጣ ሰው

የህይወት ቡድኑ በተራ ቁጥር 1-2-5 ና 6 ባሉት አራት ሰዎች ሊጀመር ይችላል፡፡





## አንድ - ለአንድ + ትንሹ ቡድን = የህይወት ቡድን፡፡

በርካታ ሰዎች በዳይናሚክ መሰረታዊና በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ከሰለጠኑ በኋላ የመጀመሪያው የህይወት ቡድን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ከፊተኛው ገፅ ላይ በስዕሉ እንደሚታየው መሪው ተተኪውን በዳይናሚክ ማካፈል ያሰለጥነዋል፡፡ ይህ የሚሆነው አንድ ለአንድና ከቡድኑ የመሰባሰቢያ ጊዜ ውጪ ይሆናል፡፡ ቤተክርስቲያን ተመላላሽ ሆነው ድነት ያላገኙትን ሰዎች ሲጐበኙ ወንጌሉን የማካፈል ዕድል ያገኛሉ፡፡ እያንዳዱም ሰው ወደ ትንሹ ቡድን እንዲመጣ መጋበዝ ይኖርበታል፡፡ ከተጐብኚዎቹ አንዱ ድነት ካገኘ ወይም ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ከተቀበለ፣ እንደ አዲስ ክርስቲያን በዳይናሚክ መሰረታዊ እንዲሰለጥን ይበረታታል፡፡ ይህንን ኃላፊነት በተራ ቁጥር 6 የተቀመጡት ክርስቲያኖች ይወስዳሉ፡፡ ልክ የዳይናሚክ መሰረታዊ ትምህርት እንዳበቃ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ በአስተናጋጁ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ከመሪው የመሪነት ስልጠና ያጠናቀቀው ተተኪ መሪውም ዳይናሚክ ማካፈልን ስልጠናን በመስጠት ይቀጥላል፡፡

## የህይወት ቡድን ለእያንዳንዱ የቡድኑ አባል አገልግሎትን እንዲለማመድ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡

## ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደቱ ለመሪ እድገት እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ ሁኔታን ይሰጣል፡፡




### የመሪ እድገት

### ትንሹ ቡድን፡-

- የጀማሪው ቡድን(ኖች) (4-6 ሰዎች) መሪውንና ወደፊት መሪ ሊሆኑ የሚችሉ መሪዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር ያካትታል፡፡ መሪዎቹ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የተለያዩ አገልግሎት መወከል ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም አዲስ ክርስቲያንና ቤተክርስቲያን መመላለስ የሚወዱ (ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው ያልተቀበሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ) በቡድኑ ይካተቱ

### የአንድ ለአንድ አገልግሎት፡-

- መሪው ተተኪ መሪውን/ መሪዎችን በዳይናሚክ መሰረታዊ ያሰለጥናል፡፡ (ለአንድ ወር) በተጨማሪም እንዴት የህይወት ቡድኑን መምራት እንዳለበት **ለመምራት መማር - የተተኪ መሪ ስ**ልጠናን በመጠቀም ያሰለጥነዋል (አንድ ወር)
- መሪው በዳይናሚክ መሰረታዊና በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ በሰለጠኑ ወይም በግሉ ባሰለጠናቸው አልያም በወርክሾፕ በሰለጠኑ የቡድን አባላት ይጀምራል፡፡ ከዛም እነርሱን በመያዝና የተቀጣጣይ እድገት ደቀመዝሙር ማድረግ ምሳሌ በመጠቀም ሌሎችን ያሰለጥናል፤ ሰዎች ሊማሩ የሚመኙትን ችሎታ በራሳቸው ለመለማመድ ከፈለጉና በሚገባ አርአያነቱ ባለው ሰው ሲያዩ በጥሩ ሁኔታ ሊማሩ ይችላሉ፡፡

## የመሪ መጎልበት ለመብዛት ቁልፍ ነው፡፡

# በሐይል የሚንቀሳቀስ ሕይወት የአረባብ ሂደት

## የመሪ መጎልበት


መሪዎችና ደመዛሙርት እያደጉ ሲመጡ፣ እያንዳንዱ መስራች ቡድን ወደ ሁለት ወይም ሦስት የህይወት ቡድን ይረባል።

## ትንሹ ቡድን

- መሪው ቡድኑን በየሳምንቱ መምራቱን ይቀጥላል።
- ተተኪ መሪውም አሁን የራሱን ቡድን ለመምራት በየሳምንቱ ይገናኛል።

## የአንድ ለአንድ አገልግሎት

- እያንዳንዱ መሪ የራሱ/ሷ መሪ የሚኖረውና «በዳይናሚክ ማካፈል» እና ለመምራት መማር - የተተኪ መሪ ስልጠናን (በወር አንድ ጊዜ) ያሰለጥናል።
- የቡድኑ አባላት በዳይናሚክ መሰረታዊ ና በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ሌሎች ሰዎችን ያሰለጥናሉ። (ከቡድኑ የመገናኛ ሰዓት ውጪ በየሳምንቱ በመገናኘት)




ተተኪ መሪዎቹ እየተዘጋጁ ሲመጡ፣ አዳዲስ የሰለጠኑ መሪዎች አዲስ ቡድኖችን ለመምራት ይዘጋጃሉ ማለት ነው። በዚህም አገልግሎቱ ወደ ብዙ ተጨማሪ ቡድኖች እየሰፋ ይመጣል።

# ዓለማችንን ለመድረስ በመራባት መስፋፋት

# በሐይል የሚንቀሳቀስ ሕይወት ሂደት መስፋፋት


## የመሪ መጎልበት

### ትንሹ ቡድን (የመሪዎች)

- መጋቢው እንደ አሰልጣኛቸው ከቡድን መሪዎች ጋር በየወሩ ራዕይን ለመካፈል፣ መረጃ ለመለዋወጥ፣ ችግሮችን ለመፍታትና ለስልጠና «የሚመሩ መሪዎች - የህይወት ቡድን መሪ ስልጠና» የሚለውን ማሰልጠኛ በመጠቀም አብሮ ይገናኛል።

## የአንድ ለአንድ አገልግሎት፡-

- እያንዳንዱ መሪ ዳይናሚክ ማካፈልን በመያዝ ተተኪ መሪውን በግል ያሰለጥናል። (በወር አንድ ጊዜ)። በተጨማሪም ለመበረታታት፣ ለፀሎትና «ለመምራት መማር የተተኪ መሪ ስልጠና»ን በመጠቀም እንዴት ትንሹ ቡድን እንደሚመራ ለማሰልጠን ይገናኛል። (በወር አንድ ጊዜ)
- የቡድኑ አባላት በዳይናሚክ መሰረታዊ እና በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግን በመያዝ ጓደኞቻቸውንና ሌሎች ሰዎችን ያሰለጥናሉ። (ከቡድኑ የመገናኛ ሰዓት ውጪ በየሳምንቱ በመገናኘት)




አዳዲስ የህይወት ቡድን መሪዎች ይሆኑ ዘንድ የራሳቸውን ተተኪ መሪዎችን በመመልመልና በማሳደግ እራሳቸውን የሚያፈሩ መሪዎች፤ ከነዚህ አዳዲስ መሪዎች ጋር እንደ አሰልጣኞቻቸው ሆነው ሊቀጥሉ ይችላሉ።

## መባዛት ዓለምን ለመድረስ የእግዚአብሔር እቅድ ነው።

# ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት አቅም


## የመሪ መጎልበት

### ትንሹ ቡድን (የአሰልጣኞች)

- መጋቢው «አሸናፊ ቡድን - የአሰልጣኞች ስልጠና እና ለትምህርት መረጃነት የሚያገለግለውን ፅሁፍ በመጠቀም ለራዕይ ማካፈልና እቅድ ለማውጣት በየጊዜው ከአሰልጣኞች ጋር መገናኘቱን ይቀጥላል።»
- አሰልጣኞች «የሚመሩ መሪዎች - የህይወት ቡድን መሪ ስልጠና» ን በመጠቀም ለዘገባ፣ ችግሮችን ለመፍታት፣ ለፀሎት እና ለስልጠና ከህይወት ቡድን መሪዎቻቸው ጋር ይገናኛሉ።

## የአንድ ለአንድ አገልግሎት፡-


- እያንዳንዱ የህይወት ቡድን መሪ «ዳይናሚክ ማካፈል»ን በመጠቀም ተተኪ መሪውን በግል ያሰለጥነዋል (በወር አንድ ግዜ)። በተጨማሪም ለመበረታታት፣ ለፀሎትና «ለመምራት መማር - የተተኪ መሪ ስልጠና» የተሰኘውን ማሰልጠኛ መፅሀፍ በመጠቀም እንዴት ትንሹን ቡድን መምራት እንደሚችል ለማሰልጠን ይገናኛል። (በወር አንድ ግዜ)
- የቡድኑ አባላት «ዳይናሚክ መሰረታዊ» እና «ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ» ን በመጠቀም ጓደኞቻቸውንና ሌሎች ሰዎችን ያሰለጥናሉ (ከቡድኑ የመገናኛ ሰዓት ውጪ በየሳምንቱ በመገናኘት)




መጋቢውና አሰልጣኞቹ በተለያዩ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ያሉትን መሪዎች እያሰለጠኑ እያሉ፣ በተጨማሪም በአገልግሎታቸው አካባቢ የተቀጣጣይ ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን ተግባራዊ ያደርጋሉ።

# ወሰን ለሌለው እድገት መሪነት ተዋቅሯል

# ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን!
# ማፍራት በእያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አገልግሎት
# እየተከሰተ ይመጣል




## ቡድኖች <u>ሲያፈሩና</u> <u>ሲባዙ</u> በመጨረሻ ማህበረሰቡንና አለምን ለመድረሰ በቂ መስካሪ ደቀመዛሙርት እናገኛለን፡፡

# ሰርቶ ማሳያ

ማስታወሻ፡- *የመሪነት ማሰልጠኛ የመልመጃ መፅሀፍ ጥቅም እንደሚከተለው በግልፅ አሳይ፡-*

- *አንተ (የወርክሾፕ መሪ) ተተኪ መሪ ይሆን ዘንድ ከጉባኤው አንድ ሰው ምረጥና የመጀመሪያውን የህይወት ቡድን መሪ ሁን፡፡ እነደ ተተኪ መሪህ ስልጠናህን ለማሳየት ይረዳ ዘንድ* **ለመምራት መማር-የተተኪ መሪ ስልጠና** *መፅሀፍ ስጠው ፡፡*

- *ቡድንህ እያደገ ሲመጣና ተተኪ መሪህ ሲሰለጥን አዲስ የህይወት ቡድን መጀመር እንደሚቻል አስረዳ፡፡*

- *ተተኪ መሪህን (አሁን የራሱ ቡድን የህይወት ቡድን መሪ የሆነ) ይዘህ ከጉባኤው አንድን ሰው በመምረጥ የእርሱ ተተኪ መሪ እንዲሆን አድርግ፡፡ (ቡድንህን ከመጀመርህ በፊት ሁልግዜ ተተኪ መሪ ሊኖርህ ይገባል)፡፡ ለእርሱ የሚሰጠውን ስልጠናውን ለማሳየት ይረዳ ዘንድ «ለመምራት መማር - የተተኪ መሪ ስልጠና » መፅሀፍ ይሰጠው*

- *ለአንተ አዲስ የህይወት ቡድን መሪ «የሚመሩ መሪዎች - የህይወት ቡድን መሪ ማሰልጠኛ» መፅሀፍ በቀጣይነት የምትሰጠውን ስልጠናህን እንደ ቡድን መሪ ለማሳየት ይረዳ ዘንድ ስጠው፡፡*

- *የእርሱን መሪ (አሁን የራሱ ቡድን የህይወት ቡድን መሪ የሆነ) ይዘህ ከጉባኤው አንድ ሰው በመምረጥ የእርሱ ተተኪ መሪ እንዲሆን አድርግ፡፡ ለእርሱ የሚሰጠውን ስልጠናውን ለማሳየት ይረዳ ዘንድ «ለመምራት መማር - የተተኪ መሪ ስልጠና » መፅሀፍ ይሰጠው*

- *መሪህ አሁን አሰልጣኝ ነው፡፡ እናም «አሸናፊ ቡድን - የአሰልጣኖች ስልጠና ፅና ለትምህረት መረጃ የሚያገለግል መፅሀፍ» በመጠቀም ማሰልጠንህን ቀጥል፡፡ ለራሱ አዲስ የህይወት ቡድን መሪ «የሚመሩ መሪዎች - የተተኪ መሪ ስልጠና» መፅሀፍ ለእርሱ እንደ ቡድን መሪ የሚሰጠው ስልጠና ለማሳየት ይረዳ ዘንድ ይስጠው፡፡*

- *የተለያዩ መፅሀፍቶችን መሪዎቹ ከተተኪ መሪነት ወደ ህይወት ቡድን መሪነት እንደገና ወደ አሰልጣኝነት እያደጉ ሲመጡ በመሪነቱ መስመር ወደታች ማስተላለፍህን ቀጥል፡፡ ሌሎች አብያተክርስቲያናትን ደቀመዝሙር አድራጊ አበያተክርስቲያን እንዲሆኑ ለማገዝ እስከምትጠቀምበት የመጨረሻ መፅሀፍ «አልፎ መድረስ - የቤተክርስቲያ ቤተክርስቲያንን መከታተያ» ጨምሮ፡፡*

# ማጠቃለያ

## በተቀጣጣይ እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት

### የኢየሱሰ ክርስቶስን ወንጌል ለሌሎች ማካፈል

- ቤተክርስቲያን ታድጋለች ምክንያቱም ብዙ ሰዎች እየተደረሱና እየተቀናጁ ስለመጡ

### አዳዲስ ክርስቲያኖችን በክርስትና ህይወት መሰረታዊ ትምህርት ማስልጠን

- ሰዎች ደቀመዝሙር ለመሆን ይማራሉ፡፡
- ደቀመዛሙርት ሌሎችን ደቀመዝሙር እንዲያደርጉ ይዘጋጃሉ
- እያንዳዱን ትምህርት ወዲያውኑ ለሌላ አንድ ሰው በማስተላለፍ (በተቀጣጣይ እድገትደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት) በግላቸው በፍጥነት ወደ ብስለት ያድጋሉ፡፡

### ለማፍራት ይዘጋጃሉ፡፡

- ብዙ ሰዎች ደቀመዝሙር አድራጊ ይሆናሉ፡፡
- ደቀመዝሙር አድራጊዎቹ ተተኪ መሪ ለመሆን ይማራሉ እናም አንዳንዶች የህይወት ቡድን መሪ ይሆናሉ፡፡

### የመሪ መጎልበትና ወደ አገልግሎት መሰማራት

- ብዙ ሰዎችን ማሰባሰብህንና ቀጣይ ስልጠናዎችንና መዘጋጃዎችን በመስጠት ስትቀጥል መሪዎች ይገነባሉ፡፡
- የቡድን አባላት አዳዲስ ሰዎችን ስለመጋበዝና ደቀመዝሙር ስለማድረግ ይማራሉ፡፡
- የህይወት ቡድን መሪዎች ተተኪ መሪ በማሳደግና አንድ አዲስ ቡድን መውለድን ይማራሉ፡፡
- እራሳቸውን ያባዙ የህይወት ቡድን መሪዎች አሰልጣኝ ይሆናሉ፡፡
- አሰልጣኞች እንዴት የራሳቸውን የህይወት ቡድን መሪዎች ማበረታታትና ማሰልጠን እንደሚችሉ ይማራሉ፡፡
- በቤተክርስትያን ያሉ ሌሎች አገልግሎቶች የህይወት ቡድን (ትንሹ ቡድንና የአንድ ለአንድ ደቀመዝሙር ማድረጉን ሂደት) ይጀምራሉ፡፡
- የቤተክረስትያን መሪዎች የህይወት ቡድንኑን የአገልግሎት መዋቅር እንደ ቀዳሚ ደቀመዝሙር ማድረጊያ ስልት አዳዲስ ሰዎችን ለመከታተል በስራ ላይ ያውሉታል (ያዋህዱታል)፡፡
- የቤተክርስትያን አመራር ቀዳሚ ተግባር የህይወት ቡድን መሪዎችን በመርዳትና በማሰልጠን ስኬታማ እንዲሆኑ ይረዷቸዋል፡፡
- ምናልባት እግዚአብሔር አንዳንዶችን በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ ወይም በወንጌል አገልግሎት ለሙሉ ግዜ አገልግሎት ይጠራቸዋል፡፡
- ለታላቁ ተልዕኮ ዕውን መሆን ቤተክርስትያንህ በአካባቢዋና ከዛም በማለፍ ትልቅ እገዛ ታድጋለች፡፡

## *ቤተክርስቲያንህን በሐይል ወደ ተሞላ ገፅታ ለመምራት በምታደርገው ጥረት ሁሉ እግዚአብሔር ይባርክህ!*

## የአሰልጣኝ ቃል መግቢያ ቅፅ

እኔ ________________________ ክርስቶስን እና የዕርሱን ቤተክርስትያን ለማገልገል እራሴን በእግዚአብሔር ፊት እሰጣለሁ። በእኔ ስር ያሉትንና አለምን በፍቅር ለመድረስ የአገልጋይ መሪነትን አገልግሎት ለመስጠት እመኛለሁ።

አድራሻ ________________________________________________

________________________ ስልክ ቁጥር ________________________

ለቤተክርስቴያናችን እንደ አሰልጣኝ ከተመደብኩ እራሴን ለ፡-

______________________ በየቀኑ ለመፀለይ

______________________ በእምነት እንደ መፅሀፍ ቅዱስ መመሪያ ለመኖር

______________________መንፈስ ቅዱስ ህይወቴን እንዲቆጣጠር ልፈቅድ

______________________ ለጌታ አገልግሎት በመደበኛ አስራት ለማውጣት

______________________ ለቤተክረስቲያንና ለመሪዎች ታማኝና የተሰጠ ለመሆን

______________________ የአሰልጣኝ መሪዎች ስብሰባንና ስልጠና በመደበኛ ለመከታተል።

እራሴን ለመስጠት ቃል እገባለሁ

# *የምስክር ወረቀት*

ይህ የምስክር ወረቀት

ለ፡ ________________________________________________

*<u>የፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወርክሾፕን</u>*

በሚገባ ስላጠናቀቁ ተሰጥቷቸዋል።

ቀን ______________________